# ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ እግዚአብሔርን ለማገልገል መሞከር

በጸሎት መንፈስ እንደሆንን ለአፍታ ቆም እንበል። ራሶቻችንም ዝቅ እናድርግ።

ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ጠዋት ወደ እግዚአብሔር ቤት በሌላ አገልግሎት በመመለሳችን፡ ደስ ብሎናል። እኛም፡ እግዚአብሔር ሆይ፡ ከመተላለፋችን ሁሉ ዛሬ ጠዋት እንድታርመን እንጸልያለን። ልንጓዘው የመረጥከውን መንገድ አሳየን። መንገዶቹን እና መመሪያዎቹን በሙሉ ከልባችን እንድንከተል፡ ጸጋህ እና ፍቅርህ ስጠን፡ ጌታ ሆይ፡ እርሱ በቅርብ እንደሚመጣ፡ እናምናለንና፡ በዚያ ቀን፡ በክርስቶስ፡ ያለነቀፋ፡ እንገኝ ዘንድ ያደርገናል።

2 ከመምጣቱ በፊት ይፈጸማሉ ያላቸውን ምልክቶች ሁሉ፡ አሁን ሲፈጸሙ አይተናቸዋል። እናም በደስታ ያቺን ቀን እንናፍቃለን። የጥንቱ አብርሃም የተሰፋውን ልጅ ይጠባበቅ በነበረ ጊዜ፡ የእግዚአብሔር የመጨረሻዎቹ ምልክቶች በምድር ሲፈጸሙ በማየቱ፡ ልጁ እስኪመጣ ድረስ ብዙም እንደማይቆይ ተረድቶ ነበር። አሁንም እኛ ይህ እንደገና ሲደግም አይተናል። ኢየሱስ እንዲህ ብሎ ነግሮናል "ይህም ሊሆን ሲጀምር፡" ቤዛችሁ ቀርቧልና፡ አሻቅባችሁ——ራሳችሁን አንሡ፡ "የወቅቱ ጭንቀት፣ የመንግስታት ግራ መጋባት፡ በተለያዩ ቦታዎች የመሬት መንቀጥቀጥ፣ የባሕሩ ጩኸት፣ የሰው ልብ በፍርሃት መውደቅ ይሆናል።"

3 መንግስታት ምን ማድረግ እንዳለባቸው በማያውቁበት፡ በዚያ ሰዓት ውስጥ እንዳለን እንገነዘባለን። ሌላ ጦርነት እየመጣ ያለ፡ ይመስላል። ይህ እንዴት ያለ አስቃቂ ነገር ይሆናል! ምድር በመስነጣጠቅ ላይ ትገኛለች፡ የሳይንስ ሊቃውንት አንድ አስከፊ ነገር ቅርብ እንደሆነ ተናግረዋል። መጽሐፍ ቅዱስም ስለዚህ ጉዳይ ሲናገር እናያለን። እንግዲህ፡ ጌታ ሆይ፡ ዛሬ በዚህ በማረሚያው ቤት ጸንተን፡ በዚህ በጨለማው ወቅት፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ ምሪት እየተቀበልን ወደፊት መገስገስ እንድንችል፡ ብርሃን ለማብራት፡ ይህ የመጨረሻ ዕድላችን ሊሆን ይችላልና እርዳን። ይህን ሁሉ ስለ ሰሙ በኢየሱስ ስም ለመንን። አሜን።

ተቀመጡ።

4 ዛሬ ጥዋት በማደሪያው ድንኳን ውስጥ መገኘት፡ ይህን እንደ ትልቅ እድል እቆጥረዋለሁ። ለሁላችሁም የሚሆን በቂ ቦታ፡ ባለማዘጋጀታችን፡ ይቅርታ እንጠይቃችኋለን። ቦታው ተጨናንቀዋል፡ ከውጭ በየቦታው ቆመዋል።

ከውጭ ያላችሁ ሰዎች፣ ይህን ሬድዮ ላይ መስማት ትችላላችሁ። ረሳሁት... [አንድ ሰው "ከሃምሳ-አምስት እስከ ሃምሳ-ሰባት፡" አለ።——

አርታዒ።] ከሃምሳ-አምስት እስከ ሃምሳ-ሰባት። እናንተ ውጭ፡ እና በፓርኪንግ ቦታዎች፡ እና በጎዳና ላይ፡ ያላችሁ ሰዎች ይህን በሬዲዮ ላይ፡ በራዲዮ መቆጣጠርያችሁ ከሃምሳ-አምስት እስከ ሃምሳ-ሰባት መካከል መስማት ትችላላችሁ። ሞክረን የነበረው...

5 ወደዚህ የተመለስኩት፡ ምናልባት፡ ለአስር-ቀናት ያህል ስብሰባ ለማድረግ በማሰብ ነበረ፡ ስለ **ሰባቱ የመጨረሻ ወዮዎች** ለመናገር ነበረ። በእነዚያ ወዮዎች መካከል፡ መለከቶች አሉና። በቀደምም ነግሬአችኋለሁ... ስለ ሰብቱ መለከቶች በምሰብክ ጊዜ፡ ከወዮዎቹ ጋር እና ከመቅሰፍቶቹ ጋር አንድ ላይ እንደማመጣው ነግሬአችሁ ነበር። እና ጥሩ ጊዜ እንደሚሆን አሰባለሁ። ገና ከአፍሪካ እንደተመለስኩ ነው፡ እና—እና ልጆቹ የጉብኝት ጊዜያቸውን ገና አልተጠቀሙም።

ትንሹ ልጄ፡ ዮሴፍ፡ ትንሽ—ትንሽ ይቀረዋል... ንባብ ላይ ጥቂት ሳምንታት ጥናት ያስፈልገዋል። በርግጥ፡ አልፏል፡ ይሁን እንጂ በቂ አይደለም። ስለዚህ በቱክሰን አቆየነው፡ እኔ፡ አፍሪካ እያለሁ፡ የቀረውን ንባብ እያነበበ፡ ጥቂት ቀናት ትምህርት ቤት ቀጥሏል።

ከዚያም ተመልሰናል። ስለዚህ እንዲህ አሰብኩ፡ ልጆች ጉብኝት እስኪዝናኑ ድረስ፡ ከህዝቡ ጋር ጥቂት ጉባኤዎችን አድርጌ፡ እነዚህን ርዕሶች እሰብካለሁ ብዬ አሰብኩ። እዚህ ሰንደርስ ግን፡ የትምህርት ቤቱን አዳራሽ መጠቀም እንደማንችል ተረዳን።

6 የተበርናክሉ አዳራሽም ህዝቡን ለማስቀመጥ በቂ እንዳልሆነ አውቅ ነበር፣ እኔ ይህን መልዕክት በማስተላልፍበት ጊዜ... የሚጠብቁት ምኞት ላይሰማቸው ይችላል፡ ስለዚህ ሌላ ቅንጅት—ማቀናጀት ነበረብን። ልናደርጋቸው ያሰብናቸው አስር ምሽቶች ትተን—ሌላ ዕቅድ ጀመርን፡ በቃ፡ በየእሁዱ ሁለት ጉባኤዎች እንዲሆኑ አደረግኩ፡ ይህ እሁድ፡ ቀጣይ እሁድ፡ ተከታይ እሁድ፡ ሁለት ጉባኤዎች። እስከአሁን፡ ማስታወቂያ በጭራሽ አልሰራንበትም።

እናም፡ ከዚያ፡ እግዚአብሔር ከፈቀደ ስብሰባዎቹ በትምህርት ቤቱ አዳራሽ፡ በሃያ ሰምንተኛው ቀን፡ እንደሚጀምሩ በሆነ መንገድ የሰማ ካለ፡ ምናልባት፡ በሞቴሎች ውስጥ እንግዳ ማረፊያ ያስያዙ ወዳጆች ካሏችሁ፡ እ—እሰ—ሰርዘዋለሁ፡ እያችሁ፡ ምክንያቱ—ይህን ለማዘጋጀት፡ ምቹ ስፍራ ማግኘት አልቻልንም። የትምህርት ቤቱ አዳራሾች—ማግኘት አልቻሉም።

7 እና አሁን መናገር የምፈልገው፡ በእሁድ ጥዋት የወንጌል አገልግሎት ላይ ብቻ ነው። እሁድ ምሽት ለታመሙ ሰዎች ጸሎት ማድረግ እፈልጋለሁ። ለእናንተም ለታመማችሁ ሰዎች እግዚአብሔር እንደሚደርስላችሁ እናምነዋለን። ቢሊ እንዴት እንደሚያስተናግዳችሁ አላውቅም፡ የጸሎት ካርዶችን ይሰጣል፡ ብዬ አስባለሁ፡ በምንም ይሁን፡ ጉባኤውን መቆጣጠር የሚቻልባቸው መንገዶችን አስባለሁ። ነገር ግን አገልግሎት እንዲኖረን ባሰብነው በሚቀጥሉት ሶስት ሳምንታት ውስጥ ለእያንዳንዱ ሰው ለመጸለይ የምንችለውን ሁሉ እናደርጋለን። የጌታ ፈቃድ ከሆነ።

8 ከዚያም ብዙ ጊዜ የግል ቃለመጠይቆች ይኖሩብናል፡ ሰው በአንድ ነገር ወይም እንደዚህ ባለ ነገር ለአንድ ደቂቃ ሊያገኛችሁ ይፈልጋል።

እኛም እንተጋበታለን... እስኪ ሰንት ሰዎች የግል ቃለ መጠይቅ ትፈልጋላችሁ? እጃችሁን አሳዩን። ዋዉ! ማንስ ላይፈልግ ይችላል? እንግዲህ እኛም...

9 እነሱን ለማግኘት በጣም ይከብደናል፡ ስለዚህ ጥያቄአችሁን ጽፋችሁ ላኩልን፡ ለቢሊ ስጡልኝ፡ ከሱ እናገኛቸዋለን። እንግዲህ፡ አሁንም፡ ይመስለኛል፡ የጸሎት ካርድ የሚሰጥበት ሰዓት ሲደርስ፡ ማስታወቂያ ይናገራል፡ ብዬ አስባለሁ።

10 ዛሬ ጠዋት ሰንት አገልጋይ ወንድሞቻችን እዚህ አሉ? እንኳን ደህና መጣችሁ ለማለት ዕድል አላገኘንም ነበረ፡ እንጂ... አንዳቸውንም ለማለት ሞክራችኋል? ዛሬ ጠዋት ሰንት አገልጋዮች አላችሁ፡ እባካችሁ እጃችሁን ማንሳት ከቻላችሁ? ወይም፡ ቁሙ። ዛሬ ጠዋት ምን ያህል አገልጋዮች በጉባኤ ውስጥ እንዳሉ እንይ። በጣም ጥሩ፡ ደህና! ስለእነዚህ ሰዎች ጌታን አመሰግኑ። እያንዳንዳቸውን ለመለየት ጊዜ ቢኖረን እመኛለሁ፡ እንደያችኋቸው ግን እርግጠኛ ነኝ። እግዚአብሔርም... በአገልግሎታቸው ያውቃቸዋል፡ እግዚአብሔርም አብዝቶ እንዲባርካቸው እንጸልያለን። ብዙዎቹ እዚህ ለመገኘት፡ አገልግሎቶቻቸውን እንደዘጉ፡ ምንም ጥርጥር የለውም። ወንድም ጁኒየር ጃክሰን እና፡ ይመስለኛል፡ ወንድም ዶን ሩዴል፡ ይህ ሰርጭት ወደ ቤተክርስቲያናቸው እየተሰራጨ ነው። ከዚያም አልፎ፡ እንዲሁም፡ በኒውዮርክ እና በመላው አገሪቱ ባሉ ሌሎች ቦታዎችም ጭምር፣ ዛሬ ጠዋት ወደ እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን በግል ስልክ ነው እየተሰራጨ ይገኛል።

11 ወንድም ሪቻርድ ብሌየርን እዚህ በማየቴ ደስ ብሎኛል። እግዚአብሔር በዚያ በነበሩት ሰዎች መካከል ያደረገላቸውን ታላቅ ነገር በደብዳቤ አንብቤአለሁ። እኔ እንደገባኝ፡ ባለፈው ቀን... ተሳስቼ ሊሆን ይችላል፡ ወንድም ብሌየር፡ ከተሳሳትኩ፡ አርመኝ። ሥራ እየሰራ፡ ይመስለኛል፡ የሆነ ተጎታች ሽቦ ወይም ሌላ ነገር ሌላ ሰውን እያገዘ ነበር። ደብዳቤውን አንብቤዋለሁ። እናም የሆነ ነገር ገለበጡ፡ እና፡ በዚህ ምክንያት፡ ህጻን ልጅ ወደነበረበት ውኃ ውስጥ የመብራት ሽቦ ተገናኘ፡ እንደኛው... ሰውዬው—የተጎታቹ ሽቦ ባለቤት የሆነውን ልጅ፡ ህጻን ልጁ፡ ትንሽ ወንድ ልጁ ነው፡ እና ህጻኑን ገደለው። ሆዱም አበጠ። የኤሌክትሪክ ንዝረትን እናውቀዋለን፡ ማለትም፡ ሲሞቱ የሚከሰተው፡ ያ ነው። ትናንሽ ዓይኖች ተተክለዋል፡ ጥርሶቹን ነክሰዋል።

12 ወንድሞችን በጣም አስደነገጣቸው። ወንድም ብሌየር የሆነ ቦታ አግኝቶኛ፡ ለልጁ ለመጸለይ አስቦ እንደነበረ ተናግሯል፡ ይሁን እንጂ ይሄን አሰቡ፦ "ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በተሰበሰቡበት፡ በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁ።" እና አባትየው ጣቶቹን ወደ ትንሹ ልጅ አፍ ውስጥ ለማስገባት፡ በሃይል ለመክፈት እየሞከረ ጣቶቹ ተልጧል። ተንበርክከውም ስለ ታናሹ ልጅ መጸለይ ጀመሩ፡ እናም እንደገና ሕያው ሆነ።

13 ወንድም ብሌየር፡ እውነት ነበር? እዚህ ካሉ ታማኝ ወንድሞቻችን አንዱ ነው። ኦህ፡ ህጻኑ ልጅ እዚህ አለ። እሺ፡ ጌታ ይመስገን። ጥሩ ነው። ሳቢሳ፡ እስኪ እንድትነሳ እንፈልጋለን። ስለዚህ አሁን፡ የተወደደውን ጌታ በዚህ ምክንያት እናመሰግናለን። የትንሹ ልጅ አባት? አንተ አባት ነህ? ትክክል። ወንድም ሪቻርድ ብሌየር ይሄው ነው። አምላካችን ማንኛውንም ነገር ማድረግ ይችላል። የሰ፡ ስር። ቃል ገብቷል። የምንኖረው በታላቁ፡ የከበረ፡ የሰማይ አባት መለኮታዊ

መገኘት ውስጥ ነው። እና እኛም ማመን ከቻልን... የምንፈልጋቸው ነገሮች ሁሉ ይቻላል።

14 ያ ምን እንዳደረገ ተመልከቱት፣ ያ ሰው ያንን ማመን በመቻሉ ያስከፈለው ዋጋ አለን? ትንሹን ልጁን አዳነ። እግዚአብሔርም፡ ታማኝ ባርያዎች እዚያ እንዲገኙ አድርጓል... ወንድም ብሌየር እና ሌሎች፣ በዚያ ሁኔታ ውስጥ ላለ ለትንሽ ልጅ መጸለይ። አዎ፡ የሆነ ነገር ሲከሰት፡ እናንተ የሕያው የእግዚአብሔር ልጆች እንደሆናችሁ፡ አስታውሱ።

“ሁለት ወይም ከዚያ በላይ በስሜ በተሰበሰቡበት እኔ እዛ ነኝ።” ደግሞም እንዲህ ተብሎ ተጽፏል፡ “እሱ በመከራ ጊዜ ፈጣን ረዳት ነው።” መቼም ችግር አለ ቢባል፡ ትንሽ ልጅ እዚያ ወድቋል፡ በእሱ በኩል ካለፈው የኤሌክትሪክ ሞገድ የተነሳ፡ መሬት ላይ ወድቆ፡ ሞቷል። ስለዚህ በዚህ ጥዋት እግዚአብሔርን በሙሉ ልባችን፡ ስለ እነዚህ—ስላደረገልን ስለ እነዚህ ነገሮች እናመሰግናለን።

15 እነዚህን ታማኝ ሰዎችም፡ እግዚአብሔር ይባርካቸው። በድንገተኛ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር የምንመለከትበት ጊዜ ያኔ ነው። እና ወደ እርሱ ተመልከቺ፣ እናም ድንገተኛ አደጋ ከመድረሱ በፊት ከእርሱ ጋር ወዳጅነት ሁን። ይህንን እናውቃለን። በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ ካለን :እንደ ማንኛውም ወዳጅ ማንኛውንም ነገር ልንጠይቀው እንችላለን። እርሱም በመከራ ጊዜ ፈጥኖ የሚረዳ ነው።

16 የወንድም ጆን ማርቲን እህት፡ ትናንት፡ መንገድ ላይ አገኘኋት። እኔን... አንድ ሰው መንገድ ላይ አስቆመኝ፡ እና ሌላ ሰው ደግሞ አልፎ እጁን እውለበለበልኝ። ወደ ቤት ስትመለሱ፡ እንደው፡ ሰዎችን በየቦታው፡ ሲጨባበጡ፡ እና የመሳሰሉትን ነገሮች ታያላችሁ። እና ስለ እኚህ ሴት፡ በቅርቡ ደውለውልኝ እንደነበር አስታውሳለሁ፡ አንድ ሰው ከኋላዋ፡ በመኪና፡ አከርካሪዋን ከላይ-እስከ-ታች መታት። ቀሪ ሕይወቷ ሽባ ሊያደርጋት ነበር። ዛሬ ጠዋት በእግዚአብሔር መገኘት እየተባረከች፡ በሰብሰባ ላይ ተገኝታለች። ቢሮ ውስጥ ከእሷ ጋር እያወራሁ ነበር። ከእሷ ጋር፡ ዳግም እንድንጸልይ ፈልጌ ነበርና። እሷም... እዚህ አንዱ ቦታ ነች። ተመልሳ መግባት የቻለች አይመስለኝም።

እንደውም፡ ይኸው፡ በትክክል፡ አጠገባችን ተቀምጣለች። ትክክል። እህቴ፡ ምናልባት ለሰዎቹ፡ አንድ ደቂቃ ቁሚላቸው እስኪ... ዶክተሩ ከጥቂት ቀናት በፊት፡ በፍፁም መራመድ እንደማትችል የተናገረላት፡ እመቤት ይህች ናት፡ የሰብራት—ሰብራት፡ የተሰበረ አከርካሪ እና ሌላ ሌላ። አሁን ግን ሙሉ ጤነኛ ሆና፡ እነሆ ቆማለች።

ታውቃላችሁ፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡ “የተፈወሰው ሰው በመካከላቸው ቆሞ ነበርና፡ ‘የሚሉትን አጥተው ዝም አሉ።” በማለት ይናገራል። እነሆ ከሞት የተመለሰው ትንሹ ልጅ፡ አከርካሪዋ የተሰበረች እመቤትም፡ እነሆ በመካከላችን ተገኝታለች። የተፈጸመ ነገር ነው፡ ስለዚህም እርሱ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እና ለዘላለም ያው ነው። የጌታ ስም የተባረከ ይሁን! አሁን በህልውናው በመኖራችን በመከራ ጊዜም ፈጥኖ የሚረዳን፡ መሆኑ ማወቃችን ምንኛ ደስተኞች መሆን አለብን።

ዛሬ ጥዋት ላይ ወንድም ቨይልን፡ ወንድም ማርቲንን፡ እና ሌሎቻችሁም በማየቴ ደስ ብሎኛል። ወንድሞቼ፡ ጌታ አብዝቶ ይባርካችሁ። አሁን ነው...

17 ከዚህ ሁሉ ሕዝብ ጋር፡ እዚህ ውስጥ ሞቹ እንዳልሆነ አውቃለሁ፡ ይሁን እንጂ በቀደም ከቱክሰን ሰወጣ፡ መቶ አራት ወይም መቶ አምስት ያህል ነበር። ወደ እኩለ ሌሊት ገደማ፣ ዘጠና-ሶስት ነበር፡ ለእኔ በጣም ጥሩ ሆኖ ይሰማኛል። እናም በፓርከር አርብ ቀን ከመሄዳችን በፊት፡ አንድ መቶ አርባ ነበር አሉ። እና ምን ያህል ሞቃት እንደሆነ መገመት ትችላላችሁ። እርግጥ፡ ያ ማለት ምድረ በዳ ነው።

18 እና፡ አሁንም፡ ቀጣይ ሶስት እሁዶች። ዛሬ፡ በአሰራ አምስት፡ ይመስለኛል፡ አይደል፡ ወይም በአሰራ ሰድስት፡ በአሰራ አምስት፡ ነው አይደል? በአሥራ ስምንት፡ እና በሃያ ስምንት፡ እና ነሐሴ አንድ፡ (ልክ ነው አይደል? ) ነሐሴ። በሃያ-አምስት... በአሥራ ስምንት፡ በሃያ-አምስት፡ እና በአንድ፡ በተበርናክል ውስጥ አገልግሎቶች ይኖራሉ። እንደው፡ ታውቃላችሁ፡ አብዛኛው ውጪ ይገኛል ምክንያቱም፡ አያችሁ፡ ውስጥ ያለውን፡ እዚህ ያለውን አሁን፡ ከውስጥ፡ ታውቃላችሁ ማዳረስ አልቻልንም፡ አሁን ደግሞ የባሰ ነው። ከቻላችሁ ተመልሳችሁ ኑ።

19 ሌላው ባለአደራዎችን ጋር ስብሰባ ለማደረግ ፈልጌአለሁ። እንዳደርግ በሚሰማኝ ጊዜ፡ እንዲህ ባለ ቦታ ስብሰባ እንዳላካሂድ ከሚያደርጉኝ ነገሮች ተላቅቄአለሁ። ስለዚህ የራሳችን ድንኳን ገዝተን—በመትከል፡ መቆየት አንችልም ወይ ብዬ፡ ለመጠየቅ አሰቤአለሁ። እዚህ ቦል ፓርክ ውስጥ፡ ወይም በእርሻ ቦታ ላይ ተክለን፡ እንደ ጌታ ምሪት፡ ከቦታ ወደ ቦታ ማንቀሳቀስ እንችላለን። ወደፊት ለማድረግ ያሰብነው ነገርም ይህ ነው። አያችሁ፡ ያን በተመለከተ ራዕይ አለን። ይህ የሆነበት ምክንያትም ምናልባት ለዚህ ይመስለኛል... ይኸውላችሁ፡ አንዳንዴ፡ ነገሮች ስለከሰቱ መጥፎ ነገር ነው ብለን እናሰባለን፡ ይሁን እንጂ፡ ምናልባት፡ ወደዚህ አይነት ነገሮች እንድትደርሱ የሚመራችሁ፡ እግዚአብሔር ሊሆን ይችላል፡ አያችሁ። እርሱ፡ አደርጋለሁ ካለ፡ ያደርገዋል።

20 ከጥቂት ምሽቶች በፊት፡ ብዙዎቻችሁ፡ ወደ አፍሪካ ከመሄዳችን ከአንድ ወር ገደማ በፊት፡ **የሙሽራ አመራረጥ**፡ በሚል ርዕስ፡ በካሊፎርኒያ የተሰብከ ካሴት ነበር፡ ምናልባት ብዙዎቻችሁ፡ ካሴቱን አግኝታችኋል። የቅጂው መጨረሻዎቹ ደቂቃዎች፡ በካሴቱ ውስጥ መኖራቸውን በጭራሽ አላስታውሰም። የጌታ መንፈስ ግን የመጣው በዚህ መንገድ ነው። ወንጌሉ በፊታቸው ከተሰበከና ከታወጀ በኋላ፡ ሰለ አኗኗራቸው እና ሰለስራቸው አውግዣቸዋለሁ። ያን ጊዜም፡ በድንገት፡ መንፈስ ቅዱስ ተናገረ እንዲህም አለ፡ “ቅፍርናሆም፡” አያችሁ፡ “አንቺ በመላእክት ሰም የምትጠሪ ከተማ ሆይ፡” ሎስ አንጀለሰን ነው፡ “ወደ ሰማያት ከፍ ከፍ ብለሻል፥ ወደ ሲኦልም ትወርጃለሽ።” አያችሁ? ካለቀ በኋላም፡ እኔ፡ ውጭ ነበርኩ፡ ወንድም ሞሰሊ እና ቢሊ ከእኔ ጋር ነበሩ። እነርሱም... ወደ ኋላ ሄደው ተመለከቱ፡ እና ወለሉ በሙሉ በሰው ተሞልቶ ነበር፡ አገልጋዮች እያለቀሱ ነበር።

21 እኔም ሄጄ ቃሉን አገኘሁት። “መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰለዚህ ጉዳይ አንድ ነገር አለ፡” አልኳቸው።

ኢየሱስ የጎበኟቸው የባህር ዳርቻ ከተሞችን ሁሉ እና ቅፍርናሆምን፡ መገሰጹ ነው። እንዲህ፡ ብሎ ተናገረ፡ “ቅፍርናሆም ሆይ፡ ወደ ሰማያት ከፍ ከፍ

አልሽን፡ ወደ ሲኦል ትወርጃለሽ።” “በአንቺ የተደረገው ሥራ በሰዶምና በገሞራ ተደርጎ ቢሆን፡ ዛሬ በተነሱ ነበር፡” አለ። በዚያን ጊዜም፡ ሰዶምና ገሞራ ከባሕር በታች ነበሩ።

እና ከዚያ በኋላ፡ ከኢየሱስ ትንቢት፡ ምናልባት ከአንድ መቶ ዓመት በኋላ፡ እርሱ የጎበኛት ብቸኛዋ የባህር ዳርቻ ከተማ ቅፍርናሆም፡ በመሬት መንቀጥቀጥ በባሕሩ ውስጥ ሰመጠች። ያም ለካሊፎርኒያ፡ ለሎስ አንጀለስ ቀጥተኛ መልስ እንደሆነ እወቁ።

22 በቀደም በቱክሰን፡ ልክ እንደተመለስኩ፡ ታላቅ የመሬት መንቀጥቀጥ ተከሰቷል። ሳይንቲስቶች በቴሌቪዥን ላይ እየሳሉት ነበር። ጋዜጣዎች ላይ ወጥቷል። መሬቱ፡ ከአሉቲያን ደሴቶች፡ ወይም ከአላስካ ጀምሮ፡ በአሉሺያን ደሴቶች ዙርያ፡ መስንጠቅ መጀመሩን፡ ከባህር እስከ ሁለት መቶ ማይልስ ርቀት፡ በሳንዲያጎ አልፎ፡ በሎስ አንጀለስ ዞሮ፡ እንደገና ሳንዲያጎ ደርሷል። እና ብዙ ኢንች ተለጥቷል። ቤቶች ፈርሰዋል። ሞቴሎች ሰጥመዋል።

ሳይንቲስቶች ሰብሰባው ላይ––ጥያቄ ቀረበላቸው። “ይህ ነገር አንድ ቀን ሊፈጸም ይችላል ወይ፡” በማለት፡ ጠየቁ?

23 “ይችላል ወይ? በደንብ!” በማለት፡ የላቫው ሳይንሳዊ ስያሜ ምን እንደሚባል ነገራቸው... በሳን ዲዬጎ ዙርያ፡ እስከ ታች ድረስ እነዚህ የመሬት መንቀጥቀጦች ያመጣው ያ ነው። ያ ጎድጎድ ያለ ቦታ ነበረ። አሁን ግን እንደሚሰምጥ አሸዋ፡ ሙሉ በሙሉ እየተሰባበረ ነው፡ የቀረው አንድ ቅርፊት ብቻ ነው። አሁን ብዙ ኢንች፡ እየተቆራረጠ ነው። ራዳርን እና ነገሮችን ወሰደው፡ ያንን ሰንጥቅ ተከትለው፡ ምልክት አድርገውበት፡ የት እንደነበረ እየተከታተሉት ይገኛሉ።

አሁንም፡ በቀደም፡ ያንን ትንቢት ከተሰጠ በኋላ፡ ከሁለት ከሶስት ቀናት በፊት፡ ተጨማሪ ብዙ ኢንቾች ተሰንጥቋል።

እና ሳይንቲሰቶችን ቃለ መጠይቅ ሲያደርጉ የነበሩትም፡ “ደህና፡ ምናልባት በእኛ ዘመን ላይሆን ይችላል፡” ብለው ተናገሩ።

24 እርሱም “በአምስት ደቂቃ ወይም በአምስት አመት ሊሆን ይችላል፡ መከሰቱ ግን የማይቀር ነው፡” አላቸው።

25 ወ/ሮ ሲምፕሰን፡ ዛሬ ከእኛ ጋር ያለች አይመስለኝም። ማለት፡ ወንድም ፍሬድ ቁጭ ብሎ አይቼዋለሁ፡ ወሮ ሲምፕሰንን ግን አላየኋትም። በ1935 ገደማ እኔ የተናገርኩትን ትንቢት፡ ወይም እንዲህ የመሰለ ነገር አገኙ፡ እና እንዲህ ይላል፡ በሆነ መጽሐፍ ውስጥ “እንዲህ ይሆናል ይላል፡” “በዚህም ባሕር አንድ ቀን ወደ ምድረ በዳው ይተምማል፡” የሚል ተጽፎ ይገኛል።

ምን እንደሚፈጠር ጠብቁ። ያ በሺዎች የሚቆጠሩ ስኩዌር ማይል ወደ ምድር ሸለቆ ውስጥ ወድቆ፡ ወደ ውስጥ ቢንሸራተት፡ በአንድ ጊዜ ሚሊዮኖች ይሞታሉ። ይህም ከባድ ማዕበልን ያስከትላል! ወደ ሳልተን ባህር ሲዘል፡ ከባህር ወለል መቶ ወይም ሁለት መቶ ጫማ ዝቅ ያለ እንደሆነ፡ አስታውሱ። ያ ውሃ ምናልባት በዚያ የማዕበል ፍጥነት፡ ወደ ቱክሰን እየተመመ ሊመጣ ይችላል። “በዚህም ባሕር አንድ ቀን ወደ ምድረ በዳው ይተምማል።”

መንግስታት እየፈረሱ፡ እስራኤል ነቅታለች፡
ነቢያቶቻችን የተነበዩትን ምልክቶች፡
የአሕዛብ ዘመን ተቈጥሮአል፡ ታጭዶ ታስሯል፡
"የተበተናችሁ ሆይ፡ ወደ ራሳችሁ፡ ተመለሱ።"

26 በመጨረሻው ዘመን ላይ ነን። ጌታ፡ አብዝቶ ይባርካችሁ። እንደጀመርኩ ሰዓቱን ረሳሁት። ለማንኛውም በፍጥነት፡ እጅግ በፍጥነት፡ ወደ ዘላለም፡ እንሰወራለን።

27 አሁን ደግሞ በቅዱስ ማርቆስ፡ ምዕራፍ 7 እና 7ኛው ቁጥር፡ በአንደኛ ዜና መዋዕል 13 ላይ ለተነበበውን ርዕሰ ጉዳይ ጽሑፍ ለማዘጋጀት ይሆናል። ለዚህ ጽሑፍ ለማዘጋጀት፣ ማርቆ 7፡7 እፈልጋለሁ።

> **... የሰውም ሥርዓት የሆነ** ትምህርት **እያስተማሩ፡ በከንቱ ያመልኩኛል።**

28 ጌታ ከሰጠኝ መልእክት በቀር፡ የማውቀው ነገር የለም፡ እኔም እሱን ብቻ እናገራለሁ። እና አሁን፡ ዛሬ ጠዋት ጥሩ ይሆናል ብዬ ባሰብኩት ርዕሰ ጉዳይ ላይ እናገራለሁ። ጌታ ቢፈቅድ ዛሬ ማታ፡ "ምግብ በትክክለኛው ዜው፡" በሚል ርዕሰ መናገር እፈልጋለሁ፡ **መንፈሳዊ ምግብ በትክክለኛው ጊዜ፡** እና እንዴት እንደምንቀበለው። አሁንም፡ ዛሬ ጥዋት፡ **ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ እግዚአብሔርን ለማገልገል መሞከር።**

29 እግዚአብሔር ሉዓላዊ ነው። በመጀመርያ ዜና መዋዕል 13 ቃል ሲነበብ፡ ዳዊት ያደረገውን ነገር እዚህ ላይ እናያለን። እንግዲህ... አሳቡ ጥሩ ነበር። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር በበጎ አሳብ መነሻነት ዋጋ አይሰጠንም። እግዚአብሔርን የምናገለግልበት መንገድ አለ፡ እርሱም ትዕዛዛቱን በመታዘዝ ፈቃዱን ማድረግ ብቻ ነው። እግዚአብሔርም ሉዓላዊ በመሆኑ፡ ምን ማድረግ እንዳለበት፡ እና እንዴት ማድረግ እንዳለበት የሚነግረው ማንም የለም። የሚያደርግበት ትክክለኛው መንገድ ያውቀዋል፡ በመንገዱም ይሰራል። ይህ ደግሞ ጥሩ ስሜት እንዲሰማኝ ያደርገኛል። ሁላችንም ጥሩ ስሜት እንዲሰማን ሊያደርገን ይገባል፡ እንደሚያደርገንም እርግጠኛ ነኝ። አንዱ በዚህ መንገድ እንዲመጣ፡ አንዱም **በዚያ** መንገድ፡ አንዱም **በሌላ** መንገድ እንዲሄድ ይፈልጋልና።

30 ስለ እግዚአብሔር፡ አንደገና፡ አንድ በጎ ነገሩ፡ እውነቱ ምን እንደሆነ፡ እና እንዴት መሰራት እንደሚገባን ሳያስታውቀን፡ አሁንም አልተወንም። እንዴት እንደሚደረግ የማናውቀውን ነገር በማድረጋችን፡ አሰናክሎ ቢቀጣን፡ ጻዲቅ ሊሆን አይችልም። እሱ እንዲህ ዓይነት አምላክ አይደለም። ቃሉን የሚናገር እና ልጆቹ እንዲያምኑት የሚጠብቅ አምላክ ነው። ስለዚህ፡ በጎ የሆነውን የሚያውቅ፡ መቼ እንደሚሰራ፡ እና እንዴት እንደሚሰራ የሚያውቅ ነው። እኛ የነገሮች ምልከታዎች አሉን፡ እሱ ግን ያውቃል።

31 ስለዚህ ሊሰራው የፈለገውን፡ አንድ ስርዓት ከዘረጋ፡ ምን እንደሚሆን እና እንዴት እንደሚከሰት ካልነገረን፡ ከዛ በኋላ፡ የሆነ ነገር ለማድረግ ስንሞክር—ብንሰናከልበት—በመሰናከላችን አንጠየቅም፡ ወይም፡ አንድ ነገር ሲሞክር፡ እያንዳንዱ አይጠየቅም። ይሁን እንጂ አንድ መንገድ አለ፡ ይህም ቃሉ ነው።

32 እና ሌላ ነገር፡ እዚህ ዳዊት፡ በልቡ መልካም ነገር ማድረግ ሲፈልግ እናየዋለን። መጥፎ አሳብ፡ ወይም መጥፎ ዓላማ አልነበረውም። ነገር ግን፡ ቤቱ፡ ወይም የጌታ ታቦት፡ ከህዝቡ መካከል—ርቆ ነበር፡ የእግዚአብሔርንም ታቦት ወደ ስፍራው ይመልስ ዘንድ ፈለገ፡ ይህም ህዝብ ሁሉ ነገሩን በፈለጉት መንገድ ማድረግ አይገባቸውም።

33 በፈንታው ግን—እግዚአብሔርን ማማከር ይገባቸው ነበር፡ እስኪ አሁን... ወንድም ብሌር እና የልጁ አባት፡ "ኧይ፡ ያሳዝናል፡ ብላቴናው ተጎዳ፡ በቃ ሞቷል። በቃ ሆኗል፡ ምን ይደረጋል ቢሉስ"? እነርሱ ግን ፈጥነው እግዚአብሔርን ፈለጉ።

34 ምስኪኗ እመቤት፡ እና ወንጌል ሰባኪው፡ ባለቤትዋ፡ ከጥቂት ምሽቶች፡ ወይም ቀናት በፊት፡ ይህች ምስኪን ሴት አከርካሪዋ በተሰበረ ጊዜ፡ ዶክተሮች... "ዕድሜ ልክ ሽባ ትሆናለች፡" ባሉ ጊዜ እነርሱ ጸንተዋል። ነገር ግን ባልየው እና እሷ "ማር፡ በደረሰብን ነገር እራሳችንን እናጽናናለን፡ ይሁን፡" ቢሉ ኖሮስ? በፍጥነት ግን አንድ ነገር አደረጉ፡ ወደ እግዚአብሔር መጡ። ሰዎች ችግር ውስጥ ሲገቡ፡ እንዴት ወደ እግዚአብሔር እንደሚደርሱ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስንት ነገሮችን ልንጠቅስ እንችላለን!

35 እንግዲህ፡ ያኔ፡ በዚያ ዘመን፡ እግዚአብሔርን የሚገናኙበት አንድ ስፍራ ብቻ ነበራቸው፡ ያም ከደሙ ስር፡ ማለት ታቦቱ ባለበት ስፍራ ነው። አሁንም ድረስ መገናኛው ከደሙ ስር፡ በታቦቱ ዘንድ ነው። የምህረት መክደኛው ለአምላኪው፡ ወይም ጸሎት አቅራቢው ሰው፡ የእግዚአብሔርን ልመና ለመጠየቅ ሲመጣ፡ ምሕረት ለመስጠት የተረጨ ነበር። ከመጀመርያ በዚህ ጉዳይ ላይ፡ እናንተ ልትሄዱበት የሚገባ፡ እግዚአብሔርም፡ የተለመደ አሰራር አለው፡ ከዚያም ውጪ ሌላ መንገድ አይቀበልም። አስቀድሞ ከተከለው አሰራር በቀር፡ ሌላ አቅርቦት አይቀበልም።

36 ብዙዎቻችሁ እንደምታስታውሱት፡ በቅርቡ አንድ መልዕክት ሰብኬ ነበር፡ ይህም፡ እግዚአብሔርን የሚያመልኩ ሰዎች የሚገናኙበት አንድ ልዩ ስፍራ አለ፡ ይህም ስፍራ እርሱ "ስሜን አኖርበታለሁ፡" ያለው ስፍራ ነው። እሱ ስሙን ያኖረባት ቤተ ክርስትያን ካገኘናት፡ ስፍራውን አግኝተናል ማለት ነው። እርሱም እንደተናገረው፡ "ስሜ በማኖርበት በር እንጂ፡ በበሮች ሁሉ ላይ አልባርካችሁም። አንድ ስፍራ ላይ አኖረዋለሁ፡ እናንተም በዚያ ታገኙኛላችሁ፡ እኔም ከእናንተ ጋር የምገናኝበት ብቸኛው ስፍራ እሱ ይሆናል።" በዚያ በኩልም፡ ስሙ ያኖረበትን ስፍራ፡ አግኝተነዋል፡ ከሚያመልከው ሰው ጋር የሚገናኝበት ብቸኛው ስፍራም ያ ነው። ስሙም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። የእግዚአብሔር ስም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

37 ኢየሱስም "በአባቴ ስም መጥቻለሁ፡" ብሏል። ልጅ ሁሉ በአባቱ ስም ይመጣልና። በአብም ስም መጣ።

"ከሰማይ በታችም ለሰዎች የተሰጠ ሌላ ስምም የለም፡" ሜቶዲስት፡ ባፕቲስት፡ ፕሪስባይቴሪያን፡ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ቢባል፡ ምንም ቢደረግ። እግዚአብሔር ከሰው ጋር የሚገናኘው አንድ መገናኛ ቦታ ብቻ ነው፡ ብቸኛ ስፍራም በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከሆነ ብቻ ነው። በብሉይ ኪዳ ስር የሚታዩ የጥንቱ ነገሮች ሁሉም፡ ይህን በጥላ ያሳያሉ። በግልጽ እንድትረዱት እፈልጋለሁ።

እንግዲህ፡ የሰንደይ ስኩል ትምህርት ነው። የተጻፉ አንዳንድ ማስታዎሻዎች እና ቅዱሳን ቃላት ይዣለአሁ። የሆነው አሮጌው ነገር ሁሉ ለእኛ ለምሳሌአችን እንደሚሆን፡ ይህ ለመረዳት እንደሚጠቅማችሁ አሰቤ ነው።

38 እንግዲህ አሁን፡ እግዚአብሔር ነገሮችን የሚያደርግበት መንገድ እንደነበረው አውቀናል። ዳዊት ግን፡ ከእግዚአብሔር እንደ ተቀባ፡ ሰለተባረከ፡ እና ሰለነገሰ፡ ብቻ በፈለግኩት መንገድ፡ ለእግዚአብሔር አንድ ነገር ማድረግ እችላለሁ ብሎ አሰበ። በዚህም ምክንያት በጭራሽ በትክክለኛው መንገድ መሄድ አልቻለም።

39 እግዚአብሔር ቃሉን የሚገልጠው በራሱ አሰቀድሞ በወሰነው ወቅት እንደሆን፡ እናሰተውላለን። እሰኪ አሁን፡ ማርቲን ሉተር የዛሬን መልእክት እንዴት ሊያውቀው ይችላል? ፕሪሰባይቴሪያኖችስ እንዴት? ማርቲንስ እንዴት ይችላል... ወይስ የካቶሊክ ቤተ ክርሰቲያን የማርቲን ሉተርን መልእክት እንዴት ልታውቀው ትችላለች? ጆን ዌሰሊስ የሉተርን መልእክት እንዴት ሊያውቀው ይችላል? ዌሰሊ የጴንጤቆሰጤውን መልእክት እንዴት ሊያውቀው ይችላል? ወይስ ጴንጤዎች ይህን መልእክት እንዴት ሊያውቁት ይችላሉ? አያችሁ? ዘር ሰለሆነ፡ ይህን በገዛ ወቅቱ ይገልጠዋል። ባደገ እና በበሰለ ጊዜ፡ እራሱን በራሱ ይገልጣል።

40 እየከፈተ እንደሚሄድ፡ እንደ ጸሐይ ሙቀት ነው። ለሰላሳና ለጋ ሆኖ፡ ዘሩን፡ ከመሬት ያጎኖቅላል፡ በመቀጠል በሌላኛው የጸሐይ እርከን፡ ቅጠሎቿን ይሰጣታል። ዘር የሚደርሰበት ወይም የሚበሰልበት ጊዜ ከሆነ... ጠንካራ ጸሐይ ይገድለዋል። ሰለዚህ፡ ቃሉን ለመገናኘት፡ ጽሐይን ይቆጣጠራል ተፈጥሮንም ያረጋጋል።

የሚኖሩበትን ወቅት ጋር ለመገናኘት፡ አሰቀድማ፡ የተወሰነችውን፡ ቤተክርሰቲያንን፡ ሙሽራይቱን፡ ያረጋጋል።

41 ዛሬ የመንግሰታት መፍረሰ፡ የምድር መሰመጥ፡ የግድግዳውን ጽሑፍ ሰንመለከት፡ ተፈጥሮ እንኳን ሳይቀር ይህን ይነግረናልና። ቤተክርሰቲያን እና ያለችበት ግዛቶች አይተናቸዋል።

ሙሽራይቱን እና ያለችበትን ግዛቶች አይተናቸዋል። እናም ከተፈጥሮ እንኳን፡ ቤተክርሰቲያን ለመሄድ እየተዘጋጀች እንደሆነ፡ እናውቃለን። እንዴት ያለ ክቡር ጊዜ ነው! ነቢያት ሁሉ ሊያዩት የናፈቁት ጊዜ፡ ይህ ጊዜ ነው።

42 ሰለዚህ፡ ቃሉን የሚገልጠው በወቅቱ ብቻ ነው። ማርቲን ሉተር እና ያነበብነው መጽሐፍ ቅዱሰ አነበበ። ዌሰሊም ማርቲን ሉተር ያነበበው ያንኑ መጽሐፍ ቅዱሰ አነበበ። ጴንጤቆሰጤዎችም እኛ የምናነበው ያንኑ መጽሐፍ ቅዱሰ ያነባሉ። ኢየሱሰም ፈሪሳውያን ያነበቡትን ያንኑ መጽሐፍ ቅዱሰ አነበበ፡ ችግራቸው ግን... በቆሎው ገና ሊደርሰ በተዘጋጀበት፡ ሳይደርሰ ለማፈሰ በመመኮራቸው፡ ዘመናቸውን መለየት አልቻሉም።

ዳዊትም እዚህ ጋር ተመሳሳይ ነገር አድርጓል።

43 እግዚአብሔር ይህንን ቃል ሊገልጥለት ለሚመርጠው ሰው፡ በወቅቱ ይገልጸዋል። ለማን እንደሚገልጥለትም እግዚአብሔር ራሱ ይመርጣል። ዓለም ሳይፈጠር በፊት መርጦ ጨርሷል። አሰቀድሞ የታወቀ ሥራው ሁሉ፡

ከሰው ተሰውሮ ነበር። በመረጠው ወቅት፡ ለተመረጠ ሰው። እሱ እንደፈቀደ ብቻ ይገልፃቸዋል። ይህን የሚሰራው፡ በተመረጠ ሰው እንጂ፡ ፓርቲም ሆነ ቡድን መርጦ አያውቅም።

44 እርሱን ለማረም፡ እና ለመናገርስ የሚዳፈር ማን ነው፡ "ጌታ ሆይ፡ **ይህን** ሰው በአገልግሎት ላይ በመሾምህ፡ ተሳስተሃል። **ይህ** ሰው እኛ እንደምናምነው አርጎ አያምንም"? እግዚአብሔርን ተሳስተሃል ብሎ ስህተቱን የሚነግረው ማን ነው? እሱን ለመናገር፡ ከእኔ በላይ ትንሽ ወንጀለኛ የሆነ ሰው ይጠይቃል። የሚሰራውን ስራ የሚያውቃልና። ማንን እንደሚመርጥ እና ማን እንደማይመርጥ፡ ምን እንደሚሰራ እና መቼ እንደሚሰራ ያውቃል። አንድን ሰው ይህንን ስራ ለመስራት ብቃት አለው ብለን ምንም ብናስበውም እንኳ፡ ለጊዜውና ለወቅቱ፡ ወይም ለዚያ ጊዜና ትክክለኛው ጊዜ ማን ብቁ እንደሆነ እግዚአብሔር ያውቃል።

45 እውነተኛው የሆነ፡ እውነተኛ ክርስቲያን፡ በእግዚአብሔር የሚያምን፡ እውነተኛው አማኝ፡ ስለ እነዚህን ነገሮች ጌታን ይጠብቃል። ጥሪ አለብኝ ብላችሁ ከተሰማችሁ፡ ከእግዚአብሔር እንደሆነ እርግጠኛ ሁኑ። አገልግሎታችሁን ጠብቁት። ትክክል መሆኑንም እርግጠኛ ሁኑ። የምትናገረው ነገር ወቅታዊ መሆኑን እርግጠኛ ሁን። መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር፦ "እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ሁሉ ኃይላቸውን ያድሳሉ። እንደ ንስር በክንፍ ይወጣሉ። ይሮጣሉ አይታክቱም። ይሄዳሉ፡ አይደክሙም" ይላል።

46 የእስራኤል ንጉስ፡ ዳዊት፡ ገና መቀባቱ እንደነበረ አስቡ። ሳሙኤልም ዘይቱን አፈሰሰበት፡ ወደፊት የእስራኤል ንጉሥ እንዲሆን፡ በእግዚአብሔር የተመረጠ ነበር። ዳዊትም የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ ዳዊት ከተማ ያመጣ ዘንድ፡ ይህን ተገለጠለት። እንግዲህ፡ ምንም ችግር አልነበረውም፡ ይሁን እንጂ፡ እንደምታዩት፡ ዳዊት በተሳሳተ መንገድ አደረገው።

47 እንግዲህ፡ እንዲህ አይነቱ ሰው መገለጥ ማግኘት ሲፈልግ፡ ማለት በእግዚአብሔር ተመርጦ ንጉስ የሆነ ሰው መቼም ከክርስቶስ ውጭ፡ በምድር ላይ ከኖሩት ታላቁ ሰው፡ ንጉስ ዳዊት እንደነበረ፡ አስባለሁ፡ ምክንያቱ፡ ክርስቶስ የዳዊት ልጅ ነውና። ይህ፡ አሁን ተቀብቶ ከእግዚአብሔር ህልውና የመጣ፡ ታላቅ ሰው፡ ለእግዚአብሔር የሆነ ነገር ለማድረግ መገለጥ አገኘ፡ እና ለእግዚአብሔር ማድረግ ፈለገ፡ መገለጡ ግን ስህተት ነበር። ይህ፡ እጅግ የሚደንቅ ነገር ነው። ርዕሰ ጉዳያችን ይዳስሳል፦ **ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ እግዚአብሔርን ለማገልገል መሞከር**።

48 አስተውሉ፡ መገለጡን ያገኘው ዳዊት ነው። መገለጡ ያገኘው፡ ነቢዩ ናታን፡ አለመሆኑን፡ አስተውሉ። መገለጡን የተቀበለው፡ ንጉሥ ዳዊት፡ ነበር። በዚህ ጉዳይ ላይ ናታንን አላማከረውም። ናታንን በጭራሽ አልጠየቀውም። ነገር ግን፡ እዚህ በአንደኛ ዜና ላይ፡ ሻለቆች፡ እና መቶ አለቆች እንዳማከረ አይታችኋልን? ናታንን ፈጽሞ አማክሮ አላማከረውም። ህዝቡን ግን አማከረ፡ የዚያን ዘመን ካህናትንና የነገረ መለኮትን ሊቃውንትን፡ ጸሐፍትንና የሃይማኖት ሊቃውንትን አማከረ። ዳዊት አስቀድሞ ተማክሮ፡ እንዲህ አለ፡ "ይህ፡ ከእግዚአብሔር፡

ከሆነ፡ እንውረድና፡ የአምላካችንን የቃል ኪዳኑን ታቦት ወደ ከተማይቱ እናውጣ፡ ነገሮችን ከማድረጋችን በፊት እግዚአብሔርን እናማክር።"

49 ነገር ግን፡ በሳኦል ዘመን አለ፡ "እግዚአብሔርን መማከርን ትተውት ነበርና፡ በ—በ—ታቦቱ፡ ማለት ኡሪም፡ ኡሪምና ቱሚም ረስተውታል። ያንን ማድረግ ረስተዋል።"

ዳዊትም አላቸው፡- "አሁን ሁላችንም፡ ወደ እግዚአብሔር እንመለስ! ወደ ትክክለኛው ነገር እንመለስ። ወርደን ታቦቱን ይዘን ወደዚህ እናምጣ፡ የእግዚአብሔርን ህልውና እናምጣ፡" በሌላ አባባል፡ "በከተማው ውስጥ። ሪቫይቫል እናድርግ። ህዝቡን እንመልስ።" ጥሩ የሚመስል፡ ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ ያልሆነ፡ መገለጥ አገኛቷል።

50 መጠየቅ የነበረበትን ምንጩን ከመጠየቅ ይልቅ፡ ገና ነገሠና፡ አለቆቹን አማከረ። ያንን የአስተሳሰብ መስመር ያዘ፡ ያንን፡ ሻለቃዎቹን እና ታላላቆቹን ተከተለ።

51 ከዚያም ወደ ሰጋዊትዋ ቤተ ክርስቲያን ገባና መነቃቃት ይችሉ እንደሆነ ጠየቃቸው። ካህናት፡ ጸሐፍት፡ የሺህ አለቆችን፡ የመቶ አለቆችን ጋር፡ ጠየቀ። "ይህ የጌታ ፈቃድ ነውን? " እነርሱም ነው አሉት። አያችሁ፡ እግዚአብሔር ሁል ጊዜ የሚጠቀምበትን ዋና ምንጭ ግን፡ ሊጠይቅ አልቻለም። አያችሁ፡ አልተረዳውም።

52 እንግዲህ አሳቡ ጥሩ ነበር። ተነሳሽነቱ ጥሩ ነበር። አላማው ጥሩ ነበር፡ ይህም ህዝቡን ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ፡ ሪቫይቫልን ወደ ከተማው ለማምጣት ነው፡ ነገር ግን እግዚአብሔር እንዲያደርግ በነገረው መንገድ አልተማከረም፡ አያችሁ፡ ሕዝቡም ሁሉና ካህናቱ፡ ንጉሡ ትክክል እንደ ሆኑ ተስማሙ፡ ታቦቱን ወደ ከተማው ለመመለስ፡ የእግዚአብሔር መገኘት ፈለጉ፡ ሪቫይቫል፡ አሁን ፈለጉ።

53 እግዚአብሔር ግን፡ ቃሉን ወቅቱ ላይ፡ ለሰዎች ለመግለጥ የገባው ቃል አልነበረውም። በዚያ ወቅት፡ ለንጉሱ እገልጥለታለሁ በፍጹም አላለም። እግዚአብሔር፡ ቅንጣት አይለወጥም። ያን አደርጋለሁ ብሎ ቃል አልገባም።

54 ምንም ያህል ቅንነት፡ እና ጥሩ ተነሳሽነት፡ ጥሩ ዓላማ ቢኖርም፡ ሰዎችም የነገሩን አስፈላጊነት ቢገነዘቡም፡ በእነዚህ ነገሮች ይፈጸም ዘንድ የሚገባው የእግዚአብሔር ፈቃድ አለ። አሰረግጬ መዳሰስ የምፈልገው ይሄን ነው፡ የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ውስጥ ቢኖር—እናንተ እንድታዩት እኔም ይህን ለማድረግ ፈልጌአለሁ። እጅግ በቀስታ እያዘገምኩ የምታዩኝ ምክንያቱ ይህ ነው። እናንተም በቴሌፎን፡ እና በመገናኛ እየተከታተላችሁ የምትገኙ ሰዎች ሆይ፡ ጊዜአችሁን ለመሻማት ሳይሆን—እንድታዩት ከመፈለጌ ነው። አሁን ጊዜ ከሌላችሁ፡ ካሴቱን ፈልጋችሁ አግኙት። ታገኙታላችሁ...

55 የቱንም ያህል ቢያስፈልግ፡ ምንም ያህል እንደሚያስፈልግ ሁሉም ቢስማማ፡ ምንም ያህል እውነት ቢሆንም፡ ገና አንድ ነገር ማወቅ ያስፈልጋል። የእግዚአብሄር ፈቃድ ነውን?

እንግዲህ፡ እግዚአብሔር ምስጢሩን ለነገሥታት እንደሚገልጥ ቃል ገብቶ አያውቅም፡ ምሥጢሩንም ለሕዝቡ እንደሚገልጥ ቃል ገብቶ አያውቅም።

56 ልክ እንደ የይምላ ልጅ፡ እንደ ሚክያስ ዘመን ነው። ሌላ ጊዜ፡ እውነቱን፡ ትክክለኛነቱን ወደ እናንተ አምጥተን ማሳየት እንድንችል፡ ከርዕሳችን ሳንወጣ፡ ይሄን ለቀቅ እናድርገው፡ እናንተም በደንብ ትይዙታላችሁ።

57 ይህ የሆነው፡ በሚክያስ ዘመን ነበር... ምስኪን ሰው ነበር፡ ደግሞ ከምስኪን ቤተሰብ የመጣ ነበር። የእስራኤል ንጉሥ፡ አክዓብ ግን፡ ከእግዚአብሔር በታች እንዳለ፡ ህዝብ፡ ትምህርት ቤት አዘጋጅቶ በሰው እጅ-ተለቅመው የተመረጡ ነብያት፡ መርጦ አመጣ፡ አራት መቶ የሚሆኑትን በአንድ ትምህርት ቤት አስገብቶ ነበር። ሰዎቹም ሐሰተኞች ነብያት አልነበሩም። ታላላቅ ሰዎች ነበሩ። ከዕብራውያን ወገን የሆኑ፡ ትክክለኛ ነብያቶች ናቸው። ጌታንም በእነዚህ ሰዎች በኩል ይጠይቅ ነበር። እነርሱም ትንቢት ይናገሩለታል። ይሁን እንጂ፡ አስተውሉ፡ ትክክለኛው የፍልሚያ ቀን በደረሰ ጊዜ፡ እያንዳንዳቸው ከእግዚአብሔር ቃል እና ፈቃድ ውጪ ነበሩ። [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።]

58 ኢዮሣፍጥም—ንጉሡን አክዓብን ሊገናኘው ከኢየሩሳሌም ወረደ፡ እነርሱም ልብሳቸውን ለብሰው፡ ወደ ውስጠኛው—መግቢያ አለፉ፡ ነቢያትን በፊታቸው አመጡ። በመጀመሪያ አክዓብ፡ “በሬማት-ዘገለዓድ የኛ የሆነ መሬት አለ፡” በማለት ተናገረ። ይህ ማለት፡ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር እንዲህ ይላል** የተባለ ነገር ነው። ኢያሱ ለሕዝቡ ከፍሎ ሰጣቸው፡ ፍልስጥኤማውያን ግን መጥተው ይዘውት ነበር።

እንዲህም አለ፡ “ልጆቻችን እንጀራ ይፈልጋሉ፡ እኛም እንጀራ የምንሰራበት በቂ መሬት የለንም። ጠላቶቻችን፡ ፍልስጤማውያንም፡ እግዚአብሔር አምላክ ከሰጠን ምድር፡ ልጆቻቸውን፡ አሕዛብን ይመግባሉ።” ፊት ለፊት በግልጽ። አለም፦ “እኛ፡ የእግዚአብሔር ሕዝብ፡ እዚህ፡ ከልጆቻችን ጋር፡ ችግረኞች ሆነናል፡ ጠላቶቻችንም እግዚአብሔር ከግብፅ ጠርቶ በሰጠን ምድር ላይ ልጆቻቸውን ይመግባሉ።” ቲኦሎጂያንን ያስንቃል፡ አይደለም’ዴ? እንዲህም አለ፦ “ሄደን እግዚአብሔር የሰጠንን ምድር እንውረሰን? ”

59 ኢዮሣፍጥም፡ “እዎ፡ እረዳሃለሁ። ወንድማማቾች ነን። አንተ በይሁዳ፡ እኔም—እኔም በእየሩሳሌም ነኝ።” ወይስ—ወይም፡ በተቃራኒው ነበር? መሰለኝ... አይ፡ ልክ ነኝ። ኢዮሣፍጥ... ይመስለኛል።

ሆኖም፡ ኢዮሣፍጥ ጌታን የሚወድ ጻድቅ ሰው፡ ንጉስ፡ መልካም ሰው ነበር። አክዓብ ግን ለብ ያለ አማኝ ነበር። አወረዷቸው፡ ኢዮሳፍጥም እንዲህ አለ፡ “ሰሙኝ፡ አስቀድመን፡ ከጌታ ጋር እንመካከር። ስለዚህ ጉዳይ ማወቅ አለብን።” አያችሁ፡ ዳዊት ኢዮሣፍጥ ያደረገውን ነገር ቢያደርግ ኖሮ! “ይህን ማድረግ የለብንምን፡” ጠየቃቸው?

አክዓብም፡ እስራኤላዊ ስለሆነ፡ ፈጥኖ እንዲህ አለ፡ “በትክክል። አራት መቶ ዕብራውያን አሉኝ፡ እንደ እኛ፡ የድርጅታችን የዕብራውያን ነቢያት ናቸው። እኔም እነርሱን አማክራቸዋለሁ። ነቢያት ናቸው።” አሁን፡ አየህ፡ እንዲሁ ነው...

60 “ነብይ፡ ያደናቅፈናል ብለህ ታስባለህ። ወንድም ብራንሃም ሆይ፡” ትላላችሁን? ኧረ፡ አዎን። በኤርምያስ ዘመን፡ ሁለት ዓመት ብቻ በግዞት ይቆያሉ ብሎ የተናገረ አንድ ሰው ነበር። ጌታ ግን ኤርምያስን፡ “ሰባ” አለው። ቀንበርም በአንገቱ ላይ አሰረ፡ ሐናንያ የተባለ ነቢዩም፡ ቀንበሩን ሰበረ።

ከዛ በኋላ የደረሰበት ግን ታውቁታላችሁ። ኧረ፡ አዎን። ከቃሉ ጋር መጽናት አለባችሁ።

ነብያቶች ሁሉ መጥተው፡ "ጌታ ከአንተ ጋር ነው! ሂድና ተከናወን፡" እያሉ፡ ትንቢት መናገር ጀመሩ።

61 ከእነርሱም አንዱ፡ አለቃቸው፡ (ስሙን አሁን ረሳሁት) ሴዴቅያስን፡ ይመስለኛል፡ ሁለት የብረት ቀንዶች ይዞ፡ መናገረር ጀመረ፡- "የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። በእነዚህ፡" እንግዲህ ሰውዬው'ኮ ቅን ሰው ነው፡ "ጠላቶችህን ወደ ምድራቸው ትመልሳለህ፡ እግዚአብሔር የሆነውን ትመልሳለህ። ለአንተም ይሰጥሃል።" ግብዝ ነበር ብዬ አላምንም። ጥሩ ሰው ነበር ብዬ አምናለሁ። ሁሉም ነቢያት እንደነበሩ አምናለሁ።

62 "ነቢያት፡" ትላለህን? አዎን! አስታውሱ፡ ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲገደል ፈቃድ የሰጠ ሰው፡ ትንቢት ተናግሯል፡ ይህም የአገልግሎቱ ሹም ስለነበረ ነው። በዚያ ዓመት ሊቀ ካህናት ነበርና። እርሱም ያንን ሹመት የያዘ ሰው ስለነበረ፡ አገልጋይ ስለነበረ፡ የእግዚአብሔርም መንፈስ ወደ እርሱ መጣ። ያ ማለት ግን ድኗል ወይም የሆነ ነገር ነው ማለት አይደለም። ቀያፋ ትንቢት ተናግሯል፡ ይህም፡ ለዚያ አገልግሎት የተሾመ ስለነበረ ነው።

63 እነዚህም ነቢያት፡ ነቢያት ሆነው፡ በነቢያት ሹመት ስለያዙ፡ ትንቢት ተናገሩ። የእግዚአብሔር መንፈስም፡ የመንፈስ ስጦታ ወዳላቸው ሰዎች ወረደ።

64 ዘጠና-ዘጠኝ በመቶ ከጴንጤቆስጤዎች ጋር እየተነጋገርኩ እንደሆነ አስባለሁ። ነገር ግን ሰዎች ብዙ ጊዜ፡ እግዚአብሔር፡ ለሰዎች ስጦታ ሊሰጣቸው ይችላል፡ አብሮ ሊሰራ ይችላል፡ሰዎች ግን በእነዚያ ሰዎች ላይ ጫና ይፈጥራሉ። ፍጹም ያልተጠሩ ከእግዚአብሔር ያልተላኩ ከሆኑ፡ ሰውየው ወይም ሴትየዋ ከፈቃዳቸው ውጪ የሆነ ነገር እንዲናገሩ ያደርጋቸዋል፡ ምክንያቱም ሰዎች ሳይወዱ ስለሚያጨናንቋቸው ነው።

65 ምስኪኑ ፓተራችንን በዚህ ጉዳይ አግኝቼው አውቃለሁ። እዚህ ጫካ ውስጥ አንድ ቀን ጠዋት፡ ከማለዳው ሦስት ሰዓት አካባቢ፡ እንዲህ አለኝ፡ "ሂድ ለወንድም ኔቪል ንገረው!" እኔም ወደ አንተ መጣሁ፡ አይደል፡ ወንድም ኔቪል?

66 ሁሉም ሰው፡ "ወንድም ኔቪል በእኔ ላይ ትንቢት ተናገር። **ይህን** ወይም **ያንን** ንገረኝ ይሉታል።" አያችሁ? እናንተም የማይፈጸሙትን ነገሮች ሲናገር ታገኙታላችሁ።

ጌታ ምን ማድረግ እንደሚፈልግ ለማወቅ፡ "የሚጠባበቁ።" አያችሁ?

67 ስለዚህ እነዚህ ሰዎች "ይህ የእኛ ነው፡" በሚል ስሜት ነገሩን በተፈጥሮአዊ ስሜት ይመለከቱታል። አያችሁ፡ እነዚህ ግን፡ የእግዚአብሔር ቃል እና ፈቃድ አልገባቸውም።

68 ሚክያስም ወረደ፡ ራእይም አይቶ ነበርና። አስተውሉ፡ በመጀመሪያ፡ መረመረ። እንዲህ አላቸው፡ "ቆዩ። ዛሬ ማታ ጊዜ ስጡኝ። ልመርምረው፡ ምናልባት ነገ ምልስ እሰጣችኋለሁ።" እንደነሱ፡ ከሌሎቹ ጋር በመስማማት፡ "የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡" ለማለት አልቸኮለም። "እግዚአብሔር የሚናገረውን ብቻ እላለሁ፡" አለ።

በማግሥቱም፡ እግዚአብሔር፡ የሚሆነውን ነገር ነገረው። ከሌሎቹም ጋር ፍጹም ተቃራኒ ነበር። ጉባኤው በሙሉ፡ የሚቃረን ነበር። በዚህም ምክንያት፡ ከመካከላቸው አንዱ ተነሥቶ ፊቱን በጥፊ መታው። እሱ ግን፡ ጠበቀ፡ አያችሁ። ከዚያም ያንን ሲያደርግ፡ ትንቢቱን እንዲሁም ራዕዩን፡ ከተጻፈው ቃል ጋር፡ አነጻጸረው፡ በቃሉ ትክክል ሆኖ አገኘው።

69 አንድ ሰው ተነስቶ ሰዎችን "'በአብ፡ በወልድና፡ በመንፈስ ቅዱስ ሰም' ለማጥመቅ መገለጥ አግኝቻለሁ ሲል፡" ከቃሉ ጋር የሚጋጭ ነው። እንዳቸውም በዚህ አላጠመቁምና። እነርሱ፡ "ኦህ፡ እኛ፡ **ለዚህ፡ ለዚያ፡** እና **ለሌላው** ነገር፡" ወዘተረፈ፡ እንጸናለን ሲሉ፡ ከቃሉ ጋር የሚጋጭ ነው። "የእባቡን ዘር አትመኑ" ሲሉ፡ ከቃሉ ጋር የሚጋጭ ነው። እነዚህ ሌሎች ነገሮች በሙሉ፡ ከቃሉ ጋር የሚቃረኑ ናቸው። ከቃሉ ጋር በወቅቱ መሆን አለበት።

70 አቤት፡ ዳዊት ያንን አድርጎት ቢሆን ኖሮ። ታቦቱ እየመጣ ነበር፡ በወቅቱ ግን፡ ስፍራ ገና አልተዘጋጀለትም ነበረ።

71 ልብ በሉ እንግዲህ ታቦቱን ሊወስዱ በወረዱ ጊዜ፡ መኳንንቱ ሁሉ እንዲህ አሉ፡ "ዳዊት፡ ማድረግ ያለብህ ነገር ይህ ነው። ክብር ለእግዚአብሔር! ሪቫይቫል ያስፈልገናል።" የዛሬ፡ እውነተኛው ጴንጤቆስጤነት ያ ነው፡ ባፕቲስት፡ ፕሪስባይቴሪያን። "ዳዊት ሆይ፡ አንተ ንጉሣችን ነህ! ሻለቃ **እከሌ-እና-እከሌ፡** እና ሜጀር **እከሌ-እና-እከሌ፡** እና ጄኔራል **እከሌ-እና-እከሌ**፡ ሁሉም... ጉባኤው ላይ ይገኛሉ። ዳዊት ሆይ፡ መደረግ ያለበት ነገር፡ ይህ ነው። አገሩ ሁሉ ከጎንህ ነው።"

ዛሬም ነገሩ ይህ ነው። እኔ አገሩን አልፈልግም። ሌላው ሁሉ ቢክደው፡ ለእኔ ግን እግዚአብሔር ይሻለኛል።

72 ዳዊትም አለቆች ሁሉ ከጎኑ ነበሩ። ከወታደራዊ-ሃይሎች ጋር ስምምነት ነበረው። ከሁሉም ቤተ-እምነቶች፡ ከሁሉም የሃይማኖት ሊቃውንት፡ ከሁሉም ጋር፡ ሁሉም ከእርሱ ጋር የሚስማሙበት ትብብር ነበረው። አክዓብ እና ሌሎችም፡ በመጽሐፍ ቅዱስ እንዲሁ ነበሩ፡ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ ነበርና፡ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር አልነበረም። ይህም እንደገባን ተስፋ አደርጋለሁ።

73 አስተውሉ፡ የቻሉትን ሁሉ ሃይማኖታዊ ነገር አድርገዋል። ምናልባት ማስታወቂያዎችን እና ሌላው ነገር ሰቅለዋል፡ "ታላቁ ሪቫይቫል! ታቦቱ ተመልሶ ሊመጣ ነው። ሪቫይቫል አዘጋጅተናል። **እንዲህ** እናደርጋለን።"

74 አስታውሱ፡ ዘማሪዎችን ልከዋል። በመሰንቆና፡ በመለከት፡ እየነፉ የሚችሉትን ያህል ሃይማኖታዊ ሥራ የሚከውኑ ሰዎችን ልከዋል፡ በዚህ ሁሉ ግን እግዚአብሔር አልነረም።

በመጠኑ ይህ ሲደገም አሁንም አይታችኋል፡ አይደል'ዴ?

75 ዘማሪዎችን በሙሉ ወሰዱ። መሰንቆ ተጫዋቾችን፡ መለከት የሚነፉትን ሁሉ፡ ሴቶች፡ ወንዶች፡ መዘመር የሚችሉትን በሙሉ ወጡ። ሁሉንም ወደዚያ አወረዷቸው፡ እና እያንዳንዱ ሃይማኖታዊ ስርዓት ሁሉ አደረጉ።

ይህን ማለት አልፈልግም፡ ግን መናገር አለብኝ። ዛሬም እነዚህ የሐይማኖት ተቋማት፡ ጴንጤዎች እና ሌሎች፡ በሃይማኖታዊ ስርዓት፡ በዝማሬ እና በጩኸት ውስጥ ይገኛሉ።

76 አስተውሉ፡ ዳዊት በሙሉ ኃይሉ ጮኸ፡ ድምጽ አወጣ፡ ዘለለ፡ አለ በሚባል ሐይማኖታዊ ስርዓት ሁሉ ተንቀሳቀሰ፡ በዚህ ሁሉ እግዚአብሔር አሁንም አልነበረም። የልቡ አሳብ፡ ዓላማው፡ እና ሌላው ነገሩ ሁሉ ትክክል ነበር፡ ይሁን እንጂ በተሳሳተ መልኩ ሄደ። አያችሁ? ሁሉንም ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎች አድርጓል፡ ጮኺል፣ ዘምሯል፣ ልዩ ዘማሪዎችን፣ ልዩ ጯኺዎችን፣ ሌሎች ነገሮች ሁሉ ነበሩት። በመንፈስ አሸበሸቡ። ሐይማኖታዊ ስርዓት ሁሉ አደረጉ።

77 እንደ ዘመናችን ታላቅ ኮንፈረንስ ያለ ነገር ነው። ዓለምን በሙሉ ለክርስቶስ እንዲሸነፍ ይጠብቃሉ። እንዲህ አይነት ነገር የለም። ታላቅ የመሬት መንሸራተት መነቃቃቶች፡ ታላላቅ ነገሮች እየተከሰቱ ነው፡ ቢያውቁ ኖሮ፡ ያ ቀን አልፏል። ተፈርዶባታል። እነርሱ ግን ህንጻዎች፡ ክሩሴዶች፡ ድርጅቶችን፡ እና ሌላ ሌላ ነገሮችን በመገንባት ላይ ናቸው። ውጤቶቹ ግን፡ በዳዊት ጊዜ እንደነበረው፡ አሁንም አልሰራም።

78 ሄደን ሪቫይቫል እናካሂዳለን። ዛሬ ዛሬ፡ አንዳንድ ታላላቅ ወንጌላውያኖቻችን፡ በስድስት ሳምታት ውስጥ፡ ሰላሳ ሺ ሰዎች ጌታን አስቀብለናል ይላሉ፡ ከአንድ ዓመት በኋላ፡ ወደ ቦታው ሲመለሱ፡ ሰላሣ አያገኙም። የሆነ ችግር አለ። ምንድነው፡ ዳዊት ያደረገው ተመሳሳይ ነገር ነው። ታላላቅ ሰዎች፡ ከበርቴዎች፡ ታላላቅ ሰባኪዎች፡ ታላላቅ ትምህርት ቤቶች፡ ባለስልጣናቶች አሉ፡ የእግዚአብሔርን ቃል ፊት ከመመልከት እና ወቅቱን ከመጠበቅ ይልቅ የሚያማክሩት ግን የሐይማኖት ተቋምን ነው። ዝም ብሎ የዓመቱን የተወሰኑ ቀናት ከመፍጀት በቀር ምግብን ማዘጋጀት አይቻላችሁም።

79 እሺ አሁን ምን እንደ ተፈጸመ እንመልከት። ምንም እንኳን... ሀይማኖታዊ ስሜታዊነታቸው እና ዝግጅቶቻቸው ሁሉ መልካም ቢሆኑም፡ የልብ ሀሳባቸው በጎ ቢሆንም፡ ኮንፈረንሶቻቸው ጥሩ ቢሆኑም፡ ዝማሬያቸው፡ ሽብሸባቸው፡ ዕልልታቸው፡ ሙዚቃቸው ሁሉ በጎ ሆኖ፡ የቃልኪዳኑ ታቦት ከእነርሱ ጋር ቢሆንም። ታቦቱ ያለ እግዚአብሔር ህልውና ምን ይጠቅማል? በቃ ሁለት የድንጋይ ጽላት የያዘ፡ የእንጨት ሳጥን ብቻ ነው።

መጠመቅ፡ የጌታን እራት እንደመካፈል ነው። አስቀድመህ ንስሓ ካልገባህ መጠመቅህ ምን ይጠቅማል? ሕይወትን ካልኖርክ፡ የቀረውን የእግዚአብሔርን ቃል ካላመንክ፡ የጌታን እራት መካፈልህ፡ ግብዝ ከመሆን ያለፈ ምን ይጠቅማል? ጥቂቱን ተቀብሎ፡ ሌላውን ማስቀረት፡ ችግር መኖሩን የሚያስረዳ ነው።

80 ታዲያ፡ እግዚአብሔርን፡ እና ወቅቱን ሰዓቱንም ያላማከለ፡ የሰዎች አመለካከት ብቻ ሲሆን፡ የሚያጋጥም ነገር፡ ምን እንደሆነ እንመለከት።

81 ብዙ ሰዎች እንዲህ ይሉኛል፦ "ለምን ወደዚህ መጥተህ ጉባኤ አታዘጋጅም? እሺ፡ እንደውልልሃለን። **ይህን፡ ያንን** ብቻ ፈርም **ሌላውን** ብቻ አድርግ፡" ይሉኛል።

ቆይ እስኪ! ምናልባት እናንተ ትፈልጉ ይሆናል፡ ጌታስ ስለሱ ምን ይላል? ብዙ ሰዎች... ተጋብዘሃል፡ ቃለመጠይቅ አለብህ፡ አመት የጠበቁ

ግላዊ መጠይቆች፡ እና ሌሎችም አሉብህ ይሉኛል። ቆይ እስኪ! ምን ማለት እንዳለብኝ ጌታ ካልነገረኝ መናገር ያለብኝን እንዴት አውቃለሁ? እያችሁ፡ መጠበቅ ነበረብኝ! “ጸፏቸው፡ እና የሚለኝን ልሰማ።” የምላችሁም ምክንያቱ ይህ ነው። እያችሁ? ቆይ’ማ! “ጌታን የሚጠባበቁ ግን ኃይላቸውን ያድሳሉ።” ልክ ነው?

82 እነዚህ ግን፡ የዘመኑ ካህናት፡ የሰነመለኮት ምሁራን፡ እና የኃይማኖት ተቋማት ብቻ አማከሩ። ካህናት፡ ጉባኤውን፡ ህዝቡን በማማከራቸውም ስህተት እንዳደረጉ ልብ በሉ፡ ህዝቡን አማክረው፡ ሣቱ።

83 ልብ በሉ፡! ታቦት ማለት ቃሉ ነበር። እውነት ነው እናውቃለን። ምክንያቱ፡ ታቦቱ ክርስቶስ ሰለሆነ፡ ክርስቶስ ደግሞ ቃል ነው። እያችሁ? የቃልኪዳኑ ታቦት፡ ወይም ቃሉ፡ በተመደበለት፡ በመጀመርያ እና ዋነኛ ሰፍራው ላይ፡ አልተቀመጠም። ኡህ፡ ቤተክርስትያን ሆይ፡ ይሄንን መረዳት እንዲያቅታችሁ!

ታላቅ ተሃድሶ እንደሚመጣ አይነት፡ ነገር ሁሉ በጣም ውብ፡ ነገር ሁሉ መልካም ነበረ፡ ይሁን እንጂ ትክክለኛውን ሰው ማማከር ሰላልቻሉ! ክሃናቱን፡ ክቡራን ሰዎችን፡ የቲኦሎጂ ምሁራንን፡ መዘምራንን፡ ከታላላቅ የጦር ድርጅቶች ጋር፡ እንዲሁም ከአገሪቱ መ—መ—መከላከያ፡ ከአገሪቱ ኃያላን ጋር መከሩ። ነገር ሁሉ ለታላቅ ጉባኤ በትክክል ተቀናጅቶ ነበር፡ አምላክን ማማከርን ግን ረሱ። አክዓብም እንዲሁ፡ ሌሎቻቸውም እንዲሁ። እንዴት ያለ ነገር ነው!

84 ይህ እንዳያመልጣችሁ። ምክር መምከር ሰላልቻሉ፡ ሊረዱት አልቻሉም። ያንን በማድረጋቸው... ተከታተሉ። እግዚአብሔር፡ በዘመኑ የላከላቸውንን ናታንን፡ እውቅናን እንኳን ሳይሰጡ፡ ወደ ካህናት ወደ ሰነመለኮት አዋቂዎች፡ ወደ ጦር ሀይል በመሄዳቸው፡ በተሳሳተ-መልኩ አደረጉት። የቃልኪዳኑን ታቦት በማንሣት በአዲስ ጋሪ ላይ አወጡት፡ በአዲስ ጋሪ ላይ አኖሩት፡ ወይም፡ “ሊጀመር ባለው በአዲስ የኃይማኖት ተቋም አኖሩት፡” ነገሩን ለመሸከም፡ በእግዚአብሔር-የተመደበውን መንገድ ረሱ። በሌዋውያን ትከሻ ላይ እንዲሸከሙት ይገባቸው ነበር። ነገር ግን፡ እያችሁ፡ ሰህተት ማደርግ ሰትጀምሩ፡ ሰህተትን ማድረግ ትቀጥላላችሁ።

85 አንዳች ጥይት ዒላማ እንድትመታ ከታለመች፡ አፈሙዙን አንድ ሺህኛ ብታነጣጥር፡ ከመጀምርያም፡ በአንድ መቶ ያርድ ውሰጥ አራት ወይም አምስት ኢንች ይሰታል። ሰለዚ በሰህተት ትጀምራላችሁ።

86 እግዚአብሔር ሆይ፡ ይህ ታላላቅ ኮንፈረንሶች ተብየዎቹ ሁሉ፡ ሲጀምሩትም በተሳሳተ መልኩ እንደጀመሩት እንድናሰተውል እርዳን። እግዚአብሔርን አላማከሩትም። በዚህ ጉዳይ ላይ የኃይማኖት ሰዎች እና ክሃናትን አማከሩ። የኃይማኖት ተቋማትን አማከሩ። “መልካም፡ **ይህ-እና-ያን** ታገኛለህን? እምናለሁ፡ ሰውን ሁሉ አንድ ማድረግ ከቻልን!” ሰውን ሁሉ ለመሰብሰብ አትሞክር። ይልቅሰ የጌታ ቃል ሰለሱ ምን ይላል በል።

87 ያንን ካደረጉም በኋላ፡ ምን እንዳደረጉ፡ ተረድተናል? ከአምላክ ቃል እና ፈቃድ ውጪ የሆነውን ያረጀ ፕሮግራሞቻቸው ለመቀጠል፡ በተደጋጋሚ ሲሄዱ እንመለከታቸዋለን። ያ ነገር ድሮ ሞቷል፡ ያረጁ የደረቁ የጥንት ነገሮች፡ ከብዙ ዓመታት በፊት ሞተዋል።

88 በጌታ በኢየሱስ ዘመንም ደርቀዋል። ሊያውቁት አልተቻላቸውም። “ሙሴንስ ብታውቁ ኖሮ፡ እኔንም ደግሞ ባወቃችሁኝ ነበር፡ ሙሴስ ስለ እኔ እንደምመጣ አስቀድሞ ተናግሯልና፡” አላቸው።

እነሱም “አባቶቻችን፡ በምድረበዳ መና በሉ” አሉት።

89 እናንተ፡ “ዕውሮች፡” ፈሪሳውያን፡ የሃይማኖት መሪዎች፡ “ሁሉም ሞተዋል!” አላቸው። “እናንተም እኔ እሱ እንደሆንኩ ባታምኑ፡ በሃጢአቶቻችሁ ትሞታላችሁ።” ይሁን እንጂ በመንገዶቻቸው ተጠምደው ስለነበሩ። ነገሩን በራሳቸው መንገድ ስለያዙት። ሊፈጽሙት አልቻሉም።

90 ዳዊትም ያደረገው በዚህ መንገድ ነው። በራሱ መንገድ፡ ነገሩን አደረገ “ምን እንደማደርግ ታውቃላችሁ? እየገሰገሰን ነው፡” አላቸው። መገለጥ አግኝቷል። “አሁን ገሰግሰናል፡ አዲስ መንገድንም እናበጃለን። የተአምራት ዘመን አልፏል፡ ስለዚህ አዲስ ተቋም እንሆናለን። አዲስ ነገር መጀመሩን እያሳያቸው፡ አዲስ ሰረገላ እንሠራለን” አለ። ምንን አይነት የውሸት ትንቢት ነው!

91 ጌታ አድርጉት ወዳላችሁ መንገድ መመለስ ይገባቿል። ሌዋውያን በትከሻቸው ላይ ይሸከሙት ነበርና፡ ያ ማለት በልብ ነው። ስለዚህ ታቦቱ፡ ወይም ቃሉ፡ በሰው ልብ እንጂ በአዲስ የሃይማኖት ተቋም፡ ወይም በአዳዲስ የሰው ሐሳቦች ላይ መሆን አይገባውም። የእግዚአብሔር ቃል ጌታ እራሱ መጥቶ በሚገለጥበት የሰው ልብ እንጂ፡ በሃይማኖት ተቋማት ውስጥ መያዝ የለበትም፡ ያም ደግሞ እግዚአብሔር መጥቶ ራሱን የሚገልጥበት ነው። በእግዚአብሔር ቃል መሰረት ከገለጠው፡ እግዚአብሔር ነው፡ ካልሆነ ግን፡ አይደለም።

እንዲሁም፡ ደግሞ፡ በዘመኑ ቃል! አዎን፡ ምናልባት ፈሪሳዊ፡ “**ይሄን** እና **ያንን** ማድረግ አትችሉም ያለ ማን ነው? እኒህ ተእዛዞች’ኮ ከሙሴ የተቀበልናቸው ትእዛዛት ናቸው።”

“ይሁን እንጂ ሙሴ ተናግሯልና... ”

ሰይጣንም አለ፡ “ለምን፡ እንዲህ ተጽፏልና፡ ‘መላእክቱን ያዛል-... ’”

92 “እንዲህ ደግሞ ተጽፏልና፡” አለ ኢየሱስ።

ወቅቱ፡ ሰዓቱ! “ሙሴንስ ብታውቁ ኖሮ! ሙሴ፡ እናንተን ከሷል’ና። ሙሴን ብታውቁት፡ እኔን ደግሞ ባወቃችሁ ነበር።” እንዲሁም አላቸው “ሙሴ ስለ እኔ ጽፎላቿልና። ‘ጌታ አምላካችሁ ከወንድሞቻችሁ መካከል እንደ እኔ ነብይ ያስነሳልና፡ እርሱንም ይሰማሉ አላቸው።’” ሙሴንስ አውቀዉት ቢሆን፡ እርሱንም ባወቁት ነበር።

93 አሁን በቅርበት፡ ተከታተሉ፡ ይህን እንዳትስቱ። በዚህ በታላቁ ኮንፈረንስ በአንድነት ለመሰብሰብ፡ በመጀመርያ፡ ከሀናቱን፡ የተከበሩትን፡ ስራዊቱን፡ ጉባኤውን፡ ጎሬቤቶቹን አማከሩ፡ ይህ ታላቅ ስብሰባ ላይ አንድ ላይ ለመሆን፡ በትክክል ሊሰሩት አልተቻላቸውም። አምላክን አላማከሩትም። ይህም በማድረጋቸው፡ ምክንያት፡ ተመልሰውም ባለማየታቸው ዘመኑን መረዳት አልቻሉም!

94 አንተ፡ ወንድም ሆይ፡ ሰማኝ። በምን አይነት ዘመን እየኖርን ነው? ዘመኑ ምንድነው? እየኖርንባት ያለችው ይህች ሰዓት ምንድን ናት? ይህ ዘመን እነርሱ እንደሚሉት የእንዲህ አይነት ዘመን አይደለም። ያ'ማ አልፏል። ፍርድ በደጅ ነው። ሲሰነጣጠቅ ማየት ትችላላችሁ። በተራራው ራስ ላይ የነበረውን አለት ታስታውሳላችሁ? የፍርድ ወቅት ነው! የሙሽራይቱን መገለጥ፡ ማለት ራዕዩን ታስታውሳላችሁ አይደል? መሰመሯን አሰጠብቃት። መሰመሯን እንድትለቅ አትፍቀድላት የሚለው።

አስተውሉ፡ "በካህናቱ ትከሻ ላይ!"

95 ዳዊት እና ካህናቱ፡ የተሻለ ነገር ማወቅ ነበረባቸው፡ ምን ነበር ግን? ካህናቱ በተሻለ መልኩ ማወቅ ነበረባቸው። ጸሐፍት፡ የነገረ መለኮት ሊቃውንት፡ የበለጠ ሊያውቁ ይገባ ነበር፡ ቃሉ ያንን እንዳይደረገ ይከለክላልና።

96 እናም ዛሬ፡ "ኢየሱስ ክርሰቶስ ትላንትናና፡ ዛሬ፡ እስከለዘለአለም ድረስ ያው አይደለም፡ ለማለት ስለፈለጉ። እእምሮን የማንበብ ብቃት ነው። **እንዲህ** ነው፡ **እንዲያ፡** ወይም **ሌላ** ነው ይላሉ።" የተሰፋውን ቃል ማየት ተሳናቸው። "ኡህ፡ ያለፈ ቀን ነው።"

ዳዊትም፡ "ኡህ፡ መልካም፡ ቆይ'ማ ቆይ። 'በ—በካህናቱ ተከሻ ላይ፡' ያ'ማ ያኔ ድሮ በሙሴ ዘመን የቀረ ነው። አዎን፡ ዛሬ፡ አዲስ መገለጥ አግኝቻለሁ። በአዲስ ጋሪ ላይ እናደርገዋለን።"

97 ካህናቱም ቀበል ያደርጉና፡ "አሜን፡ ዳዊት!" እያችሁ፡ ካህናቱ እንዲወድቁ ያደረጋቸውም ወደ አንድ ጥምረት እንዲመጡ፡ **እንዲህ** እና **እንዲያ** አድርግ በሚል በአዲሱ ኢኪመኒካል ጉባኤያቸው ተጽዕኖ ሰር መውደቃቸው፡ ካህናቱ እንዲሰናከሉ ያደረገው ያ ነው። ትክክለኛውን ሰው በፍጹም አላማከሩም። በትክክል ቅን አልሰሩም፡ ስለዚህም በችግር ላይ ወደቁ። አዎ።

98 በዚህ ዘመን፡ በብዙ ነገር እፈራለሁ... ባለፈው ማታ በቺካጎ በነበረው የሀይማኖት ቡድኖች ስብሰባ፡ አንዱ ታላቅ የተባለ የጴንጤቆስጤ አስተማሪ፡ በመካከላቸው ተነሳና፡ እኔም ስብሰባውን ከባለጉዳዮች ጋር መካፈል ነበርብኝ፡ ይሁን እንጂ አፍሪካ ላይ እሆናለሁ ብየ ሳስብ፡ ከመጀመሩ አንድ ቀን ቀደም ብሎ ደረሰኩ፡ ስለዚ አንድ ታላቅ የጴንጤቆስጤ ምሁር መረጡ'ና፡ በመካከላቸው ቆሞ ይሄ ዓለም አቀፍ የአብያተ ክርሰትያናት ጥምረት የተባለ ድርጅት ወይም ኤኪመኒካል ጉባኤ የጌታ ነገር እንደሆነ ተናገረ፡ ሁሉም እየተመለሱ ነው ብሎ ተናገረ፡ ጨምሮም ካቶሊክ ሳትቀር ወደ ኦሪጂናሉ የመጀመርያ ሁኔታዋ እንደምትመለሰ ተናገረ፡ የዲያብሎስ ወጥመድ መሆኑ ሳይረዱ፡ ማረጋገጫው ይሄ ነው በማለት፡ በአንድነት በልሳን እና ሌላ ሌላ ነገር ይናገሩ ነበር!

99 እኔ የማላውቀው፡ አንድ ሰው፡ አንዳንዴ፡ ወደፊት ምን ይሆናል ሳታውቁ ዘርን ተክላላችሁ፡ ዋና ተናጋሪው ቁጭ ባለ ጊዜ፡ የሙሉ ወንጌል አማኞች ፕረዚዳንት የሆነው ሰው ተነሳና፡ እንዲህ አለ፦ "በተናጋሪዎቻችን ላይ ቃል ላለመናገር እጠነቀቃለሁ፡ ይሁን እንጂ ወንድማን ብራንሀም ይሆናል ብሎ የነገረን እንዲህ አይደለም። ይህ ነገር ግን ወደ አውሬው ምልክት እንደሚመራን ተናግሯል" አለ።

እሱም እንዲህ አለ፡ "ወንድም ብራንሀም የሚናገርውን አያውቅም።"

"እኛ... እንደሚያውቅ እናምናለን፡" አለ። አያችሁ?

100 በቺካጎ ደግሞ፡ አልኳቸው፡ "ስንቶቻችሁ መጥቼ በዚህ ጉዳይ ያለኝ ኣመለካከት እንድሰጣችሁ ትፈልጋላችሁ? " እልልታ እና ጩኸት ጀመሩ።

አያችሁ፡ ዘርን እየዘራችሁ ነው፡ ምን እንደሚሆን አታውቁም። ብቻ መዝራታችሁን ቀጥሉበት። ጊዜው ሲደርስ፡ አንዳንዶች...

101 እንደ ቶማስ፡ ጌታ ለማየት የመጨረሻው ሰው ነበር። ይሁን እንጂ፡ ያምነው ዘንድ፡ ማየቱ ግድ ነበረ። አያችሁ፡ ሲፈጸም በሚያዩ ጊዜ። ኡህ፡ ቶማስ ገባ፡ ትንሽ ግን አርፍዶ ነበር።

102 **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል**፡ በማለት በትንቢት የተነገሩ፡ ተፈጽመው ባዩት ጊዜ፡ "ከዘይትህ ትንሽ ስጠን፡" አሉ። አያችሁ?

103 አሁን ግን፡ አስቡት፡ ተጵዕኖ ነው። አንዳንዴ ታላላቅ ሰዎች ይሰበሰባሉ። እንዲህ ሲሉ ትሰሟላችሁ፦ "ክቡር **እከሌ-እና-እከሌ፡** እና ክቡር **እከሌ-እና-እከሌ፡** የተከበሩ... " በጭራሽ አትባባሉ።

በመካከላችን ታላላቅ ሰዎች የሉም። አንድ ታላቅ ብቻ አለ፡ እርሱም እግዚአብሔር ነው። ወንድም፡ እህቶች ነን። አምስት አባላት ያሏት ቤተክርስትያን ፓስተር ብትሆንም እንኳ ምንም አይገደኝም፡ ምንም ልዩነት አይፈጥርምና፡ አየህ፡ ለእግዚአብሔር ቃል ታማኝ ከሆንክ፡ ምንድም እንድትባል የሚያደርግህ ያ ነው። እንዴት፡ እና በምን ምክንያት፡ ትንሽ አለማግኘትህ አይገደኝም። እግዚአብሔር ትናንሽ ልጆች እና ትላልቅ ልጆች የሉትም። ልጆች ብቻ አሉት። ሁሉም ተመሳሳይ ናቸው።

104 አስተውሉ፡ እግዚአብሔር እንኳን፡ ከዙፋኑ ግርማ እኛን ለመምሰል ወርዷል። እንግዲህ ታልቅ ማነው? የባርያን መልክ... ለመውሰድ እንጂ፡ ካህን ለመሆን አልወረደም። የሐዋርያት እና የሌሎች እግር በማጠቡ፡ የፈጠረውን ሸክላን አጠበ። አሁንስ ታላቅ ማን ነው?

105 እነዚህ ሰዎች ግን፡ ተጵዕኖ ስር ወደቁ። አልገባቸውም። አዲስ ነገር ይሆናል ብለው አሰቡ፡ አይሆንም፡ ጌታ ይሆናል ያላለው ነገር ግን ሊሆን ነበር። በተሳሳተ መንገድ ሄደዋልና።

ያ ሁሉ መጓጓት ለዚህ ነበር፡ ያኔ... ገና ከጅምሩ፡ ሲጀምሩ፡ እያንዳንዱ የሃይማኖት ተቋም የራሱ መለኮታዊ ፈዋሽ ይዘዋል፡ እያንዳንዱ የሃይማኖት ተቋም **ይህን፡ያንን፡** ወይም **ሌላ** ይዘው ነበር። እያንዳንዱ የሃይማኖት ተቋም የየራሳቸው ዳዊትም አላቸው። በየግላቸው **ይሄን፡ ያን፡** ወይም **ሌላ** ነበራቸው። የሆነውን ነገር አይታችኋል? እዚህ የሚደረጉ ነገሮች ሁሉ ያኔም ተደርጓል። ያው ነው። ተጵዕኖ!

106 ለሚኖሩበት ዘመን የተላከላቸውን፡ ወቅታዊው ቃል፡ ተቃወሙት።

107 አስተውሉ፡ እነኚህን ነገሮች ለማከናወን፡ "የሌዋውያን ትከሻ፡" ከአምላክ የተሰጠ እውነተኛ መንገድ ነበር። "ታቦቱን ሌዋውያን ይሸከሙ።" ከዛ ውጪ የሆነ የትኛውም ነገር ተቃራኒ ነው። እግዚአብሔር አይለዋወጥም። እርሱ እንድተናገረው፡ እንዲሁ ነው። ከቃሉ ጋር መወገን ያለባችሁ፡ ለዚህ ነው! አዎን፡ ማስታወሻ መያዝ ከፈለጋችሁ፡ የያዝኩት ጽሑፍ አለኝ፡ አንደኛ ዜና 15፡15። አስተውሉ።

108 ስለዚህ፡ ጌታን ስትከተሉ፡ ብጥንቃቄ ተከተሉት። በእጆምሯችሁ ልትይዙት የምፈልገው ነገር አለኝ። ስለ እግዚአብሔር አንዳች ነገር ለማድረግ፡ እግዚአብሔርን በትክክል—ለማገልገል፡ ወይም የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ለመጠበቅ፡ እግዚአብሔርን በትክክል ማገልገል ከፈለጋችሁ፡ ልታደርጓቸው የሚገባችሁ አምስት ግዴታዎች አሉ።

109 ዳዊት እግዚአብሔርን እያገለገለ ነበር። እግዚአብሔርን ከመተዉ በቀር፡ ማድረግ የሚችለውን ሁሉ እያደረገ ነበር። አያችሁ? በማድረግ ደረጃ፡ ያደረገው ነገር ለህዝቡ ጥሩ ነገር ነው፡ ለቤተክርስትያኒቱም ጥሩ ነገር አድርጓል።

110 አምስቱ ግዴታዎች፡ እነዚህን እንድታስቡ እፈልጋቿለሁ። አንድ ሰው በስራው ምንም ያህል ቅን ቢሆንም፡ እግዚአብሔርን ማገልገል ከሆነ፡ እነኚህ አምስት ግዴታዎች፡ በግድ መኖር አለባቸው።

አንደኛው፡ ያንን ለመደረግ ጊዜው መሆን አለበት።

111 ለምሳሌ—ሙሴ ተነሰቶ፡ "እኛም መርከብ ሰርተን፡ በናይል ወንዝ በላይ እንንሳፈፋለን፡" ቢልስ? በኖህ ዘመን መርከብን መሰራት ወቅቱ ነው፡ በሱ ወቅት ግን ሊሆን አይችልም።

112 ኢየሱስ ራሱ መጥቶ፡ እንዲህ ቢልስ፡ "አሁን ማድረግ ያለብንን እነግራቿለሁ። ሙሴ ወደ ተራራው እንደወጣ እኛም እንውጣና አዳዲስ የሕግ አዋጆችን እናውጅ"? አያችሁ? አሃ-ሃህ! እሱ ራሱ ግን ሕግ ነበር። አያችሁ?

113 በጊዜው መሆን አለበት። ወቅቱን መጠበቅ አለባችሁ። አሁን ገባችሁ? በጊዜው መሆን አለበት። ወቅቱ መሆን አለበት፡ ጊዜ እና ወቅት።

114 በተጨማሪም እንደተናገረው እንደ ቃሉ መሰረት መሆን አለበት። ግድ ነው። ምንም ያህል **ይህ** ሊሆን ይገባል፡ ወይም **ያንን** መሆን ይገባል፡ ወይም **ይህም** ሊሆን ይገባል ብትል አይገደኝም። ነገሩ ሁሉ እንደ ገዛ ቃሉ፡ እንደ ቀኑ እና እንደ ወቅቱ መሆን አለበት።

ሌላውም እንዲሰራው በተሰጠ ሰው መሰረት፡ መሆን አለበት።

115 ምን ያህል የተከበሩ መሆናቸው ትርጉም አይሰጠኝም። ይሄውላችሁ ንጉስ ዳዊትም፡ ልክ እንደነዚህ ሁሉ የተከበረ ነበር። የአገሪቱ ንጉስ እሱ ነበር። ይሁን እንጂ የራሱ አደራረግ ነበረው፡ እንዴት አድርጎ ሊሰራው እንደወደደም ነገራቸው። ይሁን እንጂ አልተሳካላቸውም።

116 የግድ እንደ ቃሉ፡ እንደ ዘመኑ፡ እንደ እቅዱ መደረግ አለበት።

117 እንዲሁም ይህን ሊሰራ በተመረጠ እና በተሰጠ ሰው መሆን የግድ ነው። ሙሴ "ሌላ ሰው ፈልግ ብሎ፡" ከዛ ለመሸሸ ሞከረ። እግዚአብሔር ግን ስራውን በሙሴ እንዲሰራ መረጠ። ብዙዎችም እንዲሁ፡ ጳውሎስም ለመሸሸ ሞከረ፡ ሌሎችም ብዙዎች እንዲሁ። ይሁን እንጂ በተመረጠው ሰው መሆን ግድ ይላል።

በመጀመርያ፡ ወደ ነብያት፡ መምጣት አለበት። የእግዚአብሔር ቃል ወደ ነብያት መምጣት አለበት። አሞጽ 3፡7፡ "በእውነት ጌታ እግዚአብሔር ሚስጢሩን ለባርያዎቹ ለነብያት ካልነገረ በቀር ምንም አያደርግም።" አራት።

118 እንዲሁም ነብይው በጌታ ቃል ማረጋገጫ የተባረከ መሆን አለበት።

119 አምስቱ ግዴታዎች እነዚህ ናቸው። እንዲህ መሆን አለበት። ይሆናል ሲል፡ ቀኑ፡ ወቅቱ፡ ሊሰራበት የተመረጠ ሰው፡ ወደ ነብይው መምጣት አለበት፡ ነብይው ደግሞ በጌታ ቃል ማረጋገጫ የተባረከ ነብይ መሆን አለበት። ወደ ነብይ ቢመጣም፡ ማረጋገጫ የሌላቸው ብዙዎች፡ በመጽሃፍ ቅዱስ አይተናል። የኛ ነብይ ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

120 ስለዚህ አሁን አስተውሉ፡ እዩት፡ እግዚአብሔር ሁሌም በሚሰራበት አሰራሩ አልገለጸላቸውም ነበር። እነሱ የተቀበሉት የዳዊት መንገድ ነው። የተቀበሉት የካህናቱ መንገድ ነው። የጸሐፍትን፡ የሰነ መለኮት አዋቂዎች መንገድ እንጂ፡ የእግዚአብሔርን መንገድ አልተቀበሉም። በዚያ ዘመን፡ ናታን፡ ነብይ ነበር። በኋላ፡ ናታን እንዴት እንደሚያደርጉት ነገራቸው። ነገር ግን፡ እነሆ፡ ናታንን ሳያማክሩ አድርገውታል። ናታን ተማከረ የሚል ቃል የለም። እነኛ የሚከናወኑት ታላላቅ ነገሮች፡ ተጽዕኖዎቹ ሁሉ! እና፡ አቤት፡ ያን መዝሙር ትዝ አለኝ፡ “እስኪ፡ እንቀጥል… ”

ልቦች እንዲህ ሲቀጣጠሉ፡ እርዳኝ፡ ጌታ ሆይ
ትምክህቴን ላዋርድ (ከሌሎቹ ጋር ልጓዝ)፡ ሰምህን ብቻ ልጥራው፡
ሌሎች በሚያደርጉት ነገር ላይ እንዳልተማመን አስተምረኝ፡
ከአንተ መልስ ለማግኘት በጸሎት ብቻ ልጠብቅ።

አያችሁ፡ የነገሩ አደራረግ መንገድ ይህ ነው። በትክክለኛው መንገድ ሲከናወን ልየው፡ ከዛ በኋላ ይታመናል።

121 እግዚአብሔርም፡ ነገሩን የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡ በሚል ጸጋ ባለው በናታን ሳይሆን፡ ነገሩን በዳዊት፡ እና በአገልጋዮች፡ እንዲሁም በህዝቡ፣ በሺህ አለቆች እና **በመቶ አለቆች ገለጸላቸው።** ጌታም ነገሩን፡ ከሁሉ በፊት፡ ለዘመኑ ነብይ ካላሳየ በቀር ምንም እንደማያደርግ ተናግሯል። ምን እንዳደረጉ አይታቿል? በቀጥታ ከእግዚአብሔር ቃል ውጪ በመሄድ፡ የቃልኪዳኑን ታቦት አዲስ በተሰራ ጋሪ ላይ ጫኑት። አያችሁ? ስለዚህ ከጌታ ትእዛዛት እና እርሱ ከሰጠው መንገድ ውጪ ለማድረግ ሄዱ።

ወዳጆች ሆይ፡ ዛሬም እየሆነ ያለው ነገር ይህ ነው። የተለያዩ ውጤት አልባ፡ የሜዳ ላይ ኮንፈረንሶች፡ እያካሄድን የምንገኘውም ለዚህ ነው። የበዛ ቃል ኪዳን አፍራሽነት፡ የበዛ ሐጢአት፡ የበዛ… ልንገራችሁ፡ ይህች አገር ጠፍታለች፡ ይህች አገር ብቻ አይደለም፡ ሌሎች አገሮች ጭምር እንጂ። ይህች አገር፡ እንደ ጥንቷዊቷ ኢንግላንድ፡ የሌሎች አገሮች ጋለሞታ ሆናለች።

122 ከሰልጣኔ አራት መቶ ሰማንያ ማይልስ ርቃ በጫካዎች ውስጥ ባለች በሞዛምቢክ ያሉ ልቅ ልጆች፡ ሌሊቱን በሙሉ እየዘለሉ ራሶቻቸውን ወደ-ላይ-ወደ ታች እያወዛወዙ፡ ኤልቪስ ፕረስሊ ሲያዳምጡ ያድራሉ፡ እንዲህ አይነቱ፡ ነገራቸው… ወይም፡ ኤልቪስ ፕረስሊን ለማግኘት፡ ከሺ ማይልስ ርቀት ሳይቀር እስከ ሮደሺያ ድረስ፡ ይመኙታል። ደግሞም ስለሱ ሲያወሩ፡ “እሱ እና፡ ፓት ቡን፡ በጣም መንፈሳውያን ናቸው” ይላሉ። ለምን፡ የዘመኑ ይሁዳ ነው፡ ነገር ግን አያውቅም። ከባዱ ነገር ደግሞ እሱ ነው፡ ትክክል ነን—ትክክል ነን ብለው ያምናሉ።

ኢየሱስ ስለ የሎዶቅያ ዘመን ሲናገርስ እንዲህ አላለምን፡ "ጎስቋላ፡ ምስኪን፡ ድሃም ዕዉርም ነህ፡ ነገር ግን አታውቀውም፡ አላለውምን? " አያውቁትም!

123 እንግዲህ፡ በአፍሪካ እና በዙርያዋ ያሉ የጴንጤቆስጤ ልጆች፡- "አዎን፡ ኤልቪስ ፕረስሊ፡ ተሰምተው የማያውቁ ድንቅ ዝማሬዎችን ዘምሯል፡" ይላሉ። ዳዊት እና ሌሎች ዘማሪዎችም፡ ያደረጉት፡ ያለ ጥርጥር ይህንኑ ነው፡ ይሁን እንጂ ማሕበሩን የሚያስመታ ሞት አምጥቷል። ወዳጆች ሆይ፡ የት እንደነበሩ እና ዛሬ የት እንዳለን፡ አይታችኋልን?

124 ያንን ስራ ለመስራት "የሌዋውያኑ ትከሻ፡" በአምላክ የተለየ የመጀመርያ ፈቃድ ነበረ። እነሱ ግን እውነተኛው መንገድ ሳያማክሩ አዲስ ጋሪን አበጁ። እንግዲህ፡ በፍጹም አይሰራም። ትክክለኛውን መንገድ አላማከሩም። አያችሁ? በጉዳዩ ላይ፡ ገፋበት፡ በተሳሳተ መስመርም ሄዱ።

125 ዛሬ ዛሬም እየሆነ ያለው ነገር ይህ ነው። ሰዎች፡ ምንም ያህል በልበ ንጹህነታቸው ቢሰሩም፡ እሱ ራሱ ነገሮችን ለመግለጽ ከሚወድበት መንገድ ውጪ ለማገልገል ሲሞክሩ፡ ሁልጊዜ ያበላሹታል። እግዚአብሔር በራሱ መንገዱ ይሰራልና። እናንተ ሰዎች፡ ምንም እንኳን ልበ ንጹሃን ብትሆኑ፡ ከመንገዱ ውጪ ብትሞክሩት፡ ነገሮችን—ታበላሻላችሁ።

126 በበልዓም ዘመን እንደተፈጸመ፡ የበልዓም ዓይነት ነገር ነው። እግዚአብሔር፡ ያንን ነብይ በልዓምን ተናገረው። ነብይ በልዓም፡ ነብይ ነበረ። ነብይ ስለነበረም፡ ቃሉ በትክክል ወደ እርሱ መጣና፡ እንዲህ አለው፡ "እነሱ የመረጥኳቸው ናቸው። ምርጦቼ ናቸው። አትሂድ" አለው።

በልዓም ግን ከከበርቴዎች፡ ከጦር አበጋዞች፡ ከሰባኪዎች፡ ከተጽዕኖ ፈጣሪዎች በመሆን፡ እንዲህ አላቸው፡ "መልካም፡ እንግዲህ—እኔ እላችኋለሁ፡ ንጉሱ... "

አያችሁ፡ ንድፋቸውን ከዳዊት ጋር፡ እና ከዚህ ዘመን ንድፍ ጋር አንድ አይነት ነው። በጥላ ለማየት ብቻ ሞክሩ፡ ታዩያላችሁ። ካያችሁት? "አሜን፡" በሉ። [ጉባኤ ሁሉ "አሜን፡" አለ።—አርታዒ።] አያችሁ፡ አያችሁ፡ ልክ እንደ አሁን ዘመን ነው።

127 ቀሳውስቱ፡ እና፡ ካ—ካ—ካህናት፡ እና ጸሀፍት እንዲሁም የስነመለኮት ምሁራን ሁሉ እንዲህ አሉ፡ "መሆን ያለበት **እንዲህ** ነው በማለት ተናገሩ።" መሆን እንዳልነበረበት ግን፡ የተረጋገጠ፡ ነበር።

128 ጌታ በልዓምን አለው፡ ነብዪም ስለነበረ፡ አስቀድሞ፡ "እንዳትሄድ፡" በማለት ነግሮታል።

129 የሌሎቹ ሰዎች ተጽዕኖ ግን እግዚአብሔር አድርግ ብሎ ካዘዘው ተቃራኒ ነገር እንዲሰራ ገፋፋው፡ በዚህም ምክንያት ሪቫይቫል ከመሆን ቀርቶ መርገም ሆነባቸው። አቤት፡ አዎን፡ ወርዶ ህዝቡን፡ እንዲህ አላቸው፡ "አሁን ቆዩ! ምን መሰላችሁ? " አላቸው፡ "እኛ'ኮ—ሞአባውያን ነን። የሎጥ ልጅ፡ ንግስታችን እንደሆነች አስታውሱ። መሰረታችን ናት። ሁላችንም ከአንድ ደም ነን። ሁላችንም... የሃይማኖት ተቋማት አንድ ነን" አላቸው። እናንተ ግን ፈጽማችሁ እንዳትተባበሯቸው። ከእንዲህ ዓይነቱ ነገር ራቁ። አያችሁ? ስለዚህ

እንዲህ አላቸው፡ “ህዝብህ እንደ ህዝቤ ነው። እንዴ፡ ሁላችንም አንድ ነን። እውነተኛ የሆነ አለም አቀፋዊት ጉባኤ እንድትኖረን፡ እርስ በእርስ፡ መጋባት እንችላለን። አያችሁ? ሁላችንም ወደ ጥንቱ ቀድሞ ስራችን ተመልሰን ዳግም አንድ መሆን እንችላለን።”

እግዚአብሔርም ስራቸውን ረገመ። ይህች ሐጢአት ከእስራኤል ይቅር አልተባለችላቸውም። በዘመናቸው ሁሉ አብራቸው ኖረች። በፍጹም ይቅርታን አላገኙም። ከሐጢአታቸው ጋራ በምድረበዳ ጠፉ። በትክክል። እግዚአብሔር በአስራሩ የመረቀላቸውን የተረጋገጠች መንገድ አልተቀበሉም።

130 አስተውሉ፡ ያደረጉት ነገር፡ እስራኤልን በምድረ በዳ በሞት እንዲጠፉ አድርጓቸዋል። ኢየሱስም “ሁሉም በሞት ጠፉ፡” ብሏል። ከሙሴ ጋር ማን እንደቆመ ተመልከቱ፡ ኢያሱና ካሌብ፡ በ—በፕሮግራሙ ውስጥ ነበሩ።

131 ዳዊት ያደረገው ነገር፡ አሁንም፡ እንደገና አስተውሉት። ያደረገው ነገር ባደረገ ጊዜ፡ ምን ተፈጠረ? ንጹህ ሰውን በሞት ሰበረባቸው።

አሁንም፡ መስመር ላይ እንደሆንን አስባለሁ፡ ስለዚህ በምድሪቱ ሁሉ እንድትሰሙኝ እፈልጋችኋለሁ።

ዳዊት ናታንን ሳያማክር፡ የእግዚአብሔርንም ቃል ሳያገኝ ያደረገው ይህን ነገር፡ ንጹሃን ሰዎችን በሞት እንዲቀጡ አሰደረገ። የሰ፡ ሰር። ታቦቱ ከቤታቸው—ሲወጣ፡ በታቦቱ መገኘት አካባቢ ይኖር ስለነበረ፡ እጁን ዘረጋበት። በሬዎቹም ይፋንኑ ነበርና፡ ታቦቱም ሊወድቅ ሲል እጆቹን ዘረጋበት።

132 ከመጀመርያም አንድ ስሕተት፡ ሁለት የተሳሳተ ነገር ፈጥረው ነበርና። በመጀመርያ፡ ናታንን አላማከሩትም። ሁለተኛ ነገርም፡ የጌታን ቃል ሳያማክሩ በመውረዳቸው ነው። ያም… በወቅቱ ሳሙኤል የጌታ ቃል ነበረና… የጌታንም ቃል በፍጹም አላማከረም። በዚህም ምክንያት፡ ያን ባደረጉ ጊዜ፡ የጌታን ቃል በሚጻረር አካሄድ ሄዱ።

ከዛ በኋላ፡ ይህ ቢሾፕ የነበረው፡ በመልካምነት ሲጠብቅ የኖረ መልካም ሰው፡ “እንደው፡ እዚህ፡ እግዚአብሔር ሲያፍር ማየት አልፈልግም፡” ብሎ በማሰብ፡ እጆቹን በታቦቱ ላይ አኖራቸው። እንደው፡ ሌዋዊ አልነበረም፡ እናም ሞተ። ሶስት ነገሮች!

133 ስለዚህ አሁን በጥንቃቄ አሰቡና፡ በዘመናችን ያሉ የሃይማኖት ተቋማትን ስራ ተመልከቱ። አያችሁ፡ “የሃሰት ትምህርት፡” በማለት ገለባብጠውታል። አያችሁ? የት እንዳሉ እዩዋቸው። አለም አቀፍ ጉባኤያቸው ያቋቁማሉ፡ እሺ። እግዚአብሔር ራሱ እውነት ያለውን፡ እውነት እንደሆነ በማረጋገጫ እያሳያቸው ሳለ፡ “አይምሮን የማምበብ ችሎታ” ነው ይላሉ። “ኡህ፡ እነዚያ እብዶች ናቸው፡” “የሚያወሩት አያውቁም፡” ይላሉ።

እውነት ነው፡ አናውቅም። ቃሉን ግን እንናገረዋለን፡ እሱ ራሱ ምን ማለት እንደሆነ ያውቀዋልና አያችሁ። እኔ ላብራራው ኣይቻለኝም፡ የሚችል ማንም የለም፡ እሱ—ራሱ—ግን ያረጋግጠዋል።

134 ስለዚ አስተውሉ። ዛሬ ዛሬ፡ ብዙ እውነተኛ እምነት ኖሮአቸው ክርስቶስን ለመከተል፡ በሙሉ ልባቸው የሚመጡትን እውነተኛ ክርስትያኖች፡ በዚሁ መልኩ መንፈሳዊ ሞት ተገድለዋል። ብዙ ልበ ቅኖች ሰዎች ክርስትያን ለመሆን

ፈልገው ወደ ካቶሊክ፣ ሜተዲስት፣ ባፕቲስት፣ ቸርች ኦፍ ክራይስት፣ እንዲሁም ጴንጤቆስጤ፣ እያችሁ፡ ክርስትያን መሆን ይፈልጋሉ፡ እጃቸውን ዘርግተው፡ ይቀላቀሏቸዋል።

135 ዳዊትም ይህን ነገር መፈጸሙን ባየ ጊዜ፡ አነቃው። ሞት ጥቃት ማድረሱን አይቶ ነበርና። ዘግይተህ አትንቃ፡ ወንድሜ።

ውጤቱን አሳዩኝ። እስኪ ይህ ሰዎችን ወደየ ቸርቹ የመለስ፡ እከሌ ተብየው-ሪቫይቫል፡ ለአገሪቱ ምን ሰራ፡ ለአማኞች—እካል ምን ጠቀመ? አዳዲስ ድርጅቶችን እና ተቋማትን ከመመስረት የዘለለ ትርጉም የለውም፡ ይህ ሁሉ መንገድ፡ አባላትን ማብዛት ወዘተ ብቻ ነው። አገሪቱስ ተሻሻለችን? እንዲህ እንዲህ ልናደርግ ነበርን ይላሉ...

136 "አሜሪካ። እግዚአብሔር አሜሪካን ይባርካት። የክርስትያን ምድር፡ ናት—አገር ናት።"

የክርስትያን ምድር ከመሆን አንድ ሚልዮን ማይል የራቀች አገር ናት እንጂ። ጸሎት እንኳን አልጸልይም ስለሷ። ለምንስ እጸልይላታለሁ፡ ጌታ በፊትዋ የገለጸው ታላቁ ሃይል እየካደች፡ በር በመዝጋት፡ እና ችላ ብላ፡ እየሄደች? እኔም ለእግዚአብሔር ሰጥቻታለሁ። ገናም ርቃ ትሄዳለች። ብቻ ምን እንደሚሆን ጠብቁ እንጂ። ገና ወደ ታች ትወርዳለች።

137 ብዙ ቅን ሰዎች፡ ወደ አንድ ድርጅት፡ ወይም ቡድን፡ ወይም አንድ ዓይነት የአምልኮ ሥርዓት ይቀላቀሉና፡ እዚያም በመንፈሳዊ ሞት ይሞታሉ። ምንም ልትነግሯቸው አትችሉም። ነገሩን ወደውስጣቸው አስርጸውባቸዋል፡ "ለምን፡ እነኚህ ቢሾፖች እንዲህ ይላሉ። **ያኛውም** እንዲህ ይላል፡ **ሌላውም** እንዲያ ይላል።" ወደ እግዚአብሔር ቃል ወሰዳችሁ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** የሚለውን ታሳዩአቸዋላችሁ። "ፓስተራችን ግን ይላሉ... "

ፓስተራችሁ ስለሚለው አይገደኝም፡ እኔ ወይም ሌላ ሰው ስለሚለው፡ ግድ አይሰጠኝም። ጌታ ከገለጸው ቃል፡ ቀን፡ ወቅት፡ እና መልዕክት፡ ወዘተ፡ የማይስማማ ከሆነ እርሱት። ከእንዲህ ዓይነቱ ነገር ራቁ። በፍርድ ቀን በሁላችሁ ፊት እቆማለሁና፡ እናንተም ታውቁታላችሁ። ሽምግልናየን እያወቅኩት፡ ትንሽየ ነገር ብናገር። እኔ... የሆነ ነገር ማወቄ አይደለም፡ ይሁን እንጂ እሱ ያውቃል። እኔ እሱ ያለኝን ሁሉ እከተላለሁ።

138 በምድሪቱ ላይ የሚዘጋጁ ታላላቅ ኮንፈረንሶችን ተመልከቷቸው። በከንቱ እንደሆኑ የታወቀ ነው። ኢየሱስ ራሱ፡ በሉቃስ 7፡7 ላይ፡ "በከንቱ ያመልኩኛል" ብሎ አልተነጋረምን? ዳዊት ታቦቱን በከንቱ አንቀሳቀሰ። እክዓብ ነብያቶቹን በከንቱ አስለጠነ። በልዓምም ገንዘብ በከንቱ ወሰደ። "የሰዎችን ትምህርትና ትዕዛዛትን እያስተማረ።" ዋናው ነገሩ የጌታ ትዕዛዝ ነው፡ ኃጥያት ምን ያህል-...

139 "እነኛ ሰዎች እኮ ቅኖች ናቸው።" ደጋግማችሁ ሰምታችሁታል፡ "በጣም ቅን ሰዎች ናቸው።" ይሁን እንጂ ትርጉም የለውም። እነ ጆሆቫ ዊትነስ፡ ሰቨን-ደይስ አድቬንቲስት፡ እና ሌሎች የኃይማኖት ድርጅቶች፡ በየጎዳናው እየዞሩ እኛ ማድረግ የማንችላቸውን ነገሮች ያደርጋሉ። ካቶሊኮችም በየጥጉ ቆመው መለመን፡ እና ልዩ ልዩ፡ እነዚህን የመሳሰሉ ድርጊቶችን ያደርጋሉ፡ ደግሞ ቢልዮን እና ቢልዮን ሲባዛ ቢልዮን ዶላሮችን አላቸው፡ ይሁን እንጂ ልመናቸውን

ይቀጥላሉ። ያለጥርጥር፡ ቅኖች ናቸው። ቸርች ይሄዳሉ—ይሰብካሉ፡ ወዘተ፡ አገልጋዮችም መድረክ ላይ ይወጣሉ አዳዲስ አባላትን ለማግኘት የሚቻላቸው ሁሉ ያደርጋሉ፡ ነገር ግን ይህም አዲስ ታቦት ነው።

ልንከተለው የሚገባን አንድ ታቦት ብቻ አለ፡ እሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው። ከዚህ ታቦት ውጪ ከሆነ ከየትኛውም ነገር ራቁ! በአዲስ ሰረገላ ላይ እንጂ፡ በእግዚአብሔር ትከሻ ላይ አይደለምና። በእውነት። ከዚህ ነገር ራቁ። በምንም መልኩ አትተባበሩት።

140 ታላላቅ ክሩሴዶቻችን፡ ቢልዮኖች እና ሚልዮኖች ጌታን ተቀብሏል። በእውነት ከነዚህ ሁሉ መካከል፡ መቶ ሰዎች መቅረታቸውን እጠራጠራለሁ። አያችሁ፡ ምንም ትርጉም የለውም።

እንግዲያውስ ወደ ተሰፋ ቃሉ ተመልከቱ።

141 የወደቀ ነገር እንደሆነ ታሰባላችሁ፡ እንደወደቀም እናውቃለንና። በምድሪቷ ያሉት አንዳንድ ታላላቅ—የተሀድሶ እንቀሳቃሾች በትክክል መውደቁን ይናገራሉ። ቤተክርስትያኒቱም የወደቀ ነገር መሆኑን ታውቃለች። ሰው ሁሉ የወደቀ እንደሆነ ያውቃል። መልካም፡ ለምንድነው? ለምን ወደቀ?

ለበጎ ነገር ነው። ሰዎችን ወደ ጌታ ህልውና ለማምጣት ነው፡ ታላላቅ ክሩሴዶች። ሚልዮኖች ሰዎችም ገንዘባቸውን ያወጣሉ፡ በታላላቅ ክሩሴዶች ላይ ያፈሱታል። ቸርቾች ሁሉ አንድ ላይ በመተባበር፡ ታላላቅ አዳራሾች ላይ፡ ታላላቅ ነገሮች ይዘጋጃል፡ ታላላቅ ነገሮችም ይከናወናሉ። ታድያ ለምን ወደቀ? ምክንያቱ'ማ የሚኖሩበት ዘመን ባለማወቃቸው ነው።

ኢየሱስ በጉንጮቹ እንባ እያፈሰ፡ በልቡ እያነባ መቆሙ። እንዲህም ማለቱ፡ አያሰደንቅም፡ "ኢየሩሳሌም፡ ኢየሩሳሌም ሆይ፡ ዶሮ ጫጩቶቿን በክንፎቿ በታች እንደምታቅፍ፡ ላቅፍሽ ስንቴ ወደድኩ አንቺ ግን አልወደድሽም! (ወደ እርሷ የላክኳቸውን ነብያት የምትወግር)፡ አሁን ግን ሰዓትሽ መጥቷል።"

142 መንፈስ ቅዱስ ከአንቺ ዘንድ ሲጮህ አትሰሚምን? "አንቺ ዩናይትድ ስቴትስ፡ አንቺም ዓለም ሆይ፡ እስከ መቼ ድረስ እሰበሰባቿለሁ፡ እናንተ ግን አልወደዳችሁም። አሁን ግን ሰአታችሁ መጥታለች። የእርካታ አምላካችሁ፡ የእርኩሰት አምላካችሁ፡ የሶዶም እና ጎመራ አምላካችሁ፡ መጥቶላቿል።" ህጻናት ልጆቻችን ሳይቀሩ፡ የቢትል ጸጉር አቆራረጥ እየተቆረጡ ጸጉራቸው ፊታቸው ላይ ያንጠለጥላሉ፡ አንዳንድ ጥቃቅን መታለሎች እየወጡ ይገኛሉ። ሴቶቻቻን ጠፍተዋል። በፍጹም መመለስ ወደማይቻልበት ሁኔታ ሄደዋል። ወንዶቻችን ጸጉሮቻቸው ከአንገታቸው በታች ለቀው፡ አጫጭር ሱሪዎች በመልበስ፡ በየመንገዱ እየዞሩ፡ እንደ ሴት እየተውረገረጉ፡ አንደኛ ሴታሴት ሆነዋል። የእግዚአብሔርን ቁጣ የሚጠባበቁ፡ ሶዶማውያን ሆነናል።

143 እንዴት እንደሚገድል፡ እንዴት እንደሚያጠፋ ታውቃላችሁ? እሱ ሁልጊዜ በሚያደርገው መንገድ። ዘማዊ ሴት ስህተት ሰትሰራ፡ በድንጋይ ተወግራ ትገደል ነበር፡ ዘማዊ ሴትን በድንጋይ ወግረው ለመግደል ድንጋይ ያነሱ ነበርና። ቤተክርስትያኒቱንም በዚሁ መልኩ ይገድላታል። መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር፡ መቶ ፓውንዶች የሚመዝኑ የበረዶ ዝናቦችን ከሰማይ አዝንቦ፡ ይወግራቸዋል ይለናል። እሱን ማን ያሰቆመዋል? የትኛውስ ሳይንስ አይሆንም ይለዋል? ያደርገዋል።

መርከብን እንደሰራ ኖህንም በደህና እንዳንሳፈፈው፡ እንደገና ለቤተክርስቲያኑ ያደርጋል።

በእራሱ ህጎች እና በራሱ መንገድ፡ ከነገሥታትና ከመቶና ከሺህ አለቆች ጋር ያመነዘረችውን ጋለሞታ በድንጋይ ይወግራታል። ባዘዘው በራሱ ሕግ፡ ወግሮ ይገድላታል። የበረዶ ድንጋይ መሥራት አትችልም ማን ይለዋል?

144 የዝናብ ነጠብጣብ እንዴት እንደሚጀምር ከሚያውቅ ሰው ጠይቁ። ክብ ይሰራና፡ ነጠብጣቦችን እየሰበሰበ፡ እየሰበሰበ የሚያስፈልገውን ክብደት እስኪያገኝ ድረስ፡ በአይን በማይታይ ፍጥነት ይሽከረከራል፡ በመጨረሻ ወደ ታች ይዘንባል።

እርሱም፡ ማለት፡ እግዚአብሔር... የምድር ስህበት ሊይዘው አልቻለምና፡ ወደ ሰማይ እንዲሁ ከፍ ከፍ አለ። የምድር ሰህበት የፈጠረ አምላክ፡ የበረዶን ድንጋይ እስከ መቶ ፓውንድ እስኪመዝን ድረስ፡ በፍጥነት እሽክርክሪት እንዲሳፈፍ ማድረግ ይቻለዋል። አደርገዋለው ብሏልና፡ ያደርገዋል። እንዳታደርግ የሚለውስ ማነው? አደርገዋለሁ ብሏልና፡ ያደርገዋል።

145 በመጨረሻ ዘመን ላይ ነን። በፍርድ አጠገብ ቆመናል። ለምን? የጴንጤቆስጤ አማኞች፡ ከሃምሳ አመታት በፊት የወረደውን መና መመገብ ይፈልጋሉ። ሆሊነስ ቸርች፡ ከሁለት መቶ አመታት በፊት የነበረውን ትሞክራለች። ሉተራኖችም፡ ሶስት መቶ፡ ወይም፡ ከዚያ በላይ አመታት፡ ከብዙ አመታት በፊት። ያረጀውን መና ለመብላት እየሞከሩ ናቸው። ወንድሜ ሆይ፡ ያ ነገር፡ በሰብሷል። ተነካክቷል። የሆነ... የሆነ ነገር—ይዟል... አዎን፡ ሁሌም ተናግሬአለሁ፡ ተምች-አለበት፡ ተልቷል። ከበላችሁት፡ ይገድላቿል።

146 ዳዊት ወይም ሌሎች የዘመኑን እንጀራ አማክረው ከነበረ እስኪ በራሳችሁ መርምሩ።

ቄሳውስቱ፡ ነብያት፡ ሰባኪዎችን፡ የስነመሎኮት ምሁራን፡ ትምህርት ቤቶች እና የሃይማኖት ተቋማት ሁሉ፡ ዘመኑን ቢያማክሩ ኖሮስ! አሁን ግን ምንም አይበጃቸውም። ገፍትረዉታልና። ምንም ነገር አይረዳቸውም። ከእንግዲህ ተጥላለች። ከንሰሓ፡ ከፍርድ እና ከምሕረት መሰመር፡ ከአምስት አመታት በፊት ገደማ ተላልፋለች።

147 አስተውሉ፡ ታድያ ምንድን ነው? ምን ሊደረግ ይችላል? ምን መደረግ አለበት? ከእርሱ ከማንጨምርበት እና ከማንቀንሰበት፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ፡ እና ከነብዪው ጋር እንማከር። ከቀነሰን ከጨመርን ግን፡ እግዚአብሔር ከህይወት መጽሐፍ ይደመሰሰናል።

መጽሐፍ ቅዱስ፡ በሚልኪያስ 4 ላይ፡ በዚህ ዘመን ሊሆን የሚገባው ነገር ይናገራል። ራእይ 10 ደግሞ፡ ሰባቱ ማህተሞች እንዴት እንደሚከፈቱ በተኃድሶ ዘመናት ሁሉ ተሰውሮ የነበረውን ሚስጢራት ሁሉ እንደሚገለጥ! እንዴት እንደሚደረግ ተናግሯል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አለ፡ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ብሏልና**። እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ፡ እውነት እንደሆነ፡ በፍፁም ለይቷል አረጋግጧል፡ በሰማይ፡ እና በጠፈር ምልክቶችና፡ ድንቆችም ሁሉ፡ ለሰላሳ-ሶስት አመታት ሙሉ፡ አረጋግጦታል።

ይሰሙታል ብላችሁ ታስባላችሁን? በጭራሽ። ሞተዋል። ነገርን ሁሉ ወደሚገድል ነገር እጆቻቸውን ዘፍቀዋልና። በጭራሽ። አይሆንም፡ ከእንግዲህ ወዲህ፡ አይሆንም።

148 ዳዊትም፡ ይህ ነገር በሆነ ጊዜ አየ። እግዚአብሔር ሆይ፡ የቆመበትን የሚያይ ዳዊትን ላክልን፡ እግዚአብሔር የገባውን ቃል፡ ዛሬ እንዴት እና በምን እንደሚያደርገው መመልከት እና ማየት የሚችል። እንዴት እንደሚያደርግ፡ እግዚአብሔር እራሱ እዚሁ በቃሉ ተናግሮታልና።

149 እግዚአብሔር ሚክያስን ነገረው። ሚክያስ ራእዩን በአራት መቶ የተከበሩ ነቢያት ፊት መረመረ። ራእዩ እውነት እንደሆነ ለማየት መረመረ። የሆነውን ለማየት፡ በፊቱ የነበረው ነብይ መለስ ብሎ ተመለከተ። መለስ ብሎ አየና፡ ኤልያስ ቆሞ፡ "አክዓብ ሆይ፡ ደምህ ውሾች ይልሱታል፡" ሲናገር፡ ተመለከተ። አሁን፡ ያየው ራእይ እንደ ጌታ ቃል መሆኑን ተመለከተና፡ አወጀው። ትክክል ነበር። በትክክል። ሌሎች የፈለጉትን ይበሉ፡ እሱ ግን ከቃሉ ጋር ጸና።

150 እንግዲያውስ በዘመናችን ያለውን ራእይ እንመለከተው። አብያተ ክርስትያናትን መገንባት ነውን፡ አዲስ ነገር ነውን፡ ታላላቅ ነገሮች ይሆናሉ ነውን? ወይስ፡ ፍርድ ነው? ወደ ኋላችሁ ተመልከቱና የዛሬውን ተሰፋ ቃል እዩ፡ ምን አይነት ዘመን ላይ እንደሆንን አስተውሉ።

151 "አየህ፡ ወንድሜ፡ ጌታ ይባረክ፡ እኔ ቅን ሰው ነኝ። ቤተክርስትያን እሄዳለሁ። ባችለር ኦፍ አርት ዲግሪ አለኝ። **ይሄን** አድርጌያለሁ፡" ትላላችሁ። ይሁን ጥሩ ነው፡ ችግር የለም፡ ምንም አልተቃወምንም፡ ዳዊትም ነበረውና፡ በዘመኑ የነበሩት ክሃናትም፡ የሰነ መለኮት ምሁራንም ሁሉ ነበራቸው። ይሁን እንጂ ቃሉን የሚጻረር ነበር።

152 ጌታ ዳግም ምን እንደሚሰራ፡ ምን እንደሚያቃና፡ እንዴት እንደሚያደርግ አስቀድሞ ተናግሯልና። በኢዩኤል 2፡28፣ የተጻፈው እውነት ነው። አቃናለሁ ብሏል። እንደሚያቃና ቃል ገብቷል። "ኩብኩባ የበላቸው አመታት ሁሉ፡" "አቃናለሁ፡" ብሏል ጌታ። ተመሳሳይ-... ትል ነው፡ አያችሁ፡ በሌላ የህይወት ደረጃ የደረሰ ትል ነው። እና ካቶሊካዊነት መብላት ሲጀምር፡ ቀጥሎ ሉተራን፡ እና ሜቶዲስት፡ እና ጴንጤቆስጤዎች፡ እና ሁሉም፡ በየተራ ሲበሉ፡ "በመጀመርያ እንደነበረች ለቤተክርስትያን አሁንም ደግሜ ሁሉን አቃናላታለሁ፡" ብሏል።

153 የበቀደሙን ራእይ አስቡት። ያችት ሙሽሪት ራሷ **ከዚህ** ጎንና፡ **በዚህ** ጎን መጣች። ከዚያ በኋላ አመንዝራዎች ልብሳቸውን ለብሰው አለፉ፡ **በዚህ** በኩል ያረጁ ነገሮቻቸው ጋር፡ ሮክ-ኤንድ-ሮል ጭፈራ እየጨፈሩ፡ ቤተክርስትያ እኛ ነን እያሉ አለፉ።

"ኧረ፡ እኛ እንዲህ አናደርግም፡" ትላላችሁ።

እግዚአብሔር አንተን የሚያይበት መንገድ ይህ ነው። እራስህን የምታየው ነገር አይደለም። እግዚአብሔር አንተን በሚያይበት መንገድ እንጂ። ማንም ሰው የራሱን ስህተት ማየት አይችልም። በእግዚአብሔር ቃል መስታወት ውስጥ ስትመለከት፡ ስህተት መሆንህን ወይም አለመሆንህን ይነግርሃል። ዳዊት ይህን ቢያደርግ ኖሮ፡ ስህተቱን ባየ ነበር። አክዓብ እንዲህ ቢያደርግ፡ ወይም ነብያት ሁሉ እንዲህ ቢያደርጉ ኖሮ፡ ስሕተታቸውን ያዩ ነበር።

154 እውነተኛው ነብይ፡ “አክዓብ ይሞታል፡ ደሙንም ውሾች ይልሱታል” አለ። ትንቢቱም በትክክል ከርሱ ጋር የሚሰማማ ነበረ። ከዛ በኋላም ትክክል መሆኑን ተረዳ። ኢዮሣፍጥም ይህን አይቶ ቢሆን ማወቅ በቻለ ነበር። ሚኪያስ ራእዩን ሲያይ'ኮ፡ በዘመኑ ከነበሩ ሰዎች ጋር ህብረት አልነበረውም፡ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** የሚል ቃል ግን ነበረው። እሱ ትክክል ነበር።

155 አሁን አስተውሉ፡ አሁን እየገባንበት ያለውን ዘመን ስንመለከት፡ በዚህ ቀን ይህን ነገር እያመጣን ነው።

ዳዊት ሊያደርገው የነበረው ነገር ምን እንደነበረም፡ አስተውሉት። በዚህ ጉዳይ ላይ ትንሽ ማስታወሻ ይዣለሁ። የቃልኪዳኑን ታቦት ወደ ራሱ የሃይማኖት ተቋም፡ ወደ ዳዊት ከተማ ሊያመጣ ነበር።

156 ያኔ በመጀመርያ ወንዝ ዳር ላይ ጌታ የተናገረውን ነገር አሰቡ፡ “መጥምቁ ዮሐንስ የፊተኛውን መምጣቱ ለማወጅ እንደተላከ... ”

ወንድሜ ሆይ፡ እነ ዩናይትዶች፡ እና አሴምብሊዎች ሁሉም፡ ይሄን ነገር አይቀበሉትም። በሌላ ሰፍራ ላይ አንድ ሊኖራቸው ግድ ነው። አሃ፡ ሁሉም እንዲህ ማድረጋቸው አይቀርም፡ አያችሁ፡ በትክክል። ሁሉም ይህን ወደ ቤታቸው ማምጣት ይፈልጋሉ።

157 ወደ ዳዊት ከተማ ማምጣት ፈለጉ። ለምን? የተዘጋጀለት ሰፋራ አልነበረም።

መልዕክቱ ወደ አንዲት ሃይማኖት ተቋም መጎተት የማይቻልበትም ምክንያት ይህ ነው። ቃሉ፡ ታቦቱ፡ ክርስቶስ፡ “ትላንትናና፡ ዛሬ፡ እስከዘለአለም ድረስ ያው የሆነውን፡” ሌሎች የሱ መገለጫዎች በሙሉ፡ ወደ ድርጅቶቻቹ ልትጎትቱ አይቻላችሁም። በጭራሽ አያምኑትም፡ ምክንያቱ ሰፍራ የለውም። መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ በሎዶቅያ ዘመን ላይ፡ ወደ ውስጥ ለመግባት ፈልጎ በውጭ ቆሞ እንዳለ ይናገር የለምን?

ምንም እንኳን ታማኝ፡ እና ታላቅ ወዘተ—ቢሆንም፡ በዳዊት ከተማ ውስጥ፡ ሰፍራ አልነበረውም። ይህም ቢሆን ሰፍራው አልነበረም። ሰፍራው በኢየሩሳሌም ነበረ። ከነብዪው ጋር ተማክረው ማድረግ የሚገባቸው ከነገራቸው በኋላ፡ የተቀመጠው በዚያ ነበርና። አያችሁ? ዳዊት ግን ወደ ከተማው ሊያመጣው ነበር። ሰፍራ ግን አልነበረውም።

158 ታቦታችን ክርስቶስ ነው፡ አይቀበሉትም። ክርስቶስ ቃል ነው፡ አይቀበሉትም። የገዛ ሰርዓታቸው፡ የሃይማኖት ተቋማቸው፡ አዲስ ታቦት፡ ወይም—አዲስ ተሸካሚ ይፈልጋሉ። የሃይማኖት ተቋማቸው፡ አዲሱን ታቦት እንዲሸከም ይፈልጉታል፡ አሃ!

አስታውሱ፡ ክርስቶስ ታቦታችን! ክርስቶስ ቃል እንደሆነ ታምናላችሁ? ስለዚህ፡ ታቦቱ ይህ ነው። ልክ ነው? መልካም። እንግዲያውስ ክርስቶስን፡ በየትኛውም የሃይማኖት ተቋም ስረገላ፡ ልትሸከሙት አትችሉም። በግል እንጂ፡ በሕብረት የሚያደርገው ነገር የለም። በግለ ሰብ ደረጃ እንጂ፡ በቡድን ደረጃ በጭራሽ ሰራውን ሰርቶ አያውቅም። አሰቀድሞ፡ አላደርግም ካለ። በኋላ ግን ካደረገ፡ የገዛ ቃሉን-ይቃወማል፡ አሞጽ 3፡7። ውሸት ልታደርገው አይቻልህም። ብጭራሽ፡ ወዲጄ። እውነት ነው።

159 ታቦቱ በድርጅት ላይ ልታወጡት አትችሉም። ምክንያቱ በዚያ ውስጥ ብዙ ራሶች ይገኛሉና። እነሱ፡ ግን፡ ሞከሩ። አያችሁ? ሊደረግ አይችልም። አላደርግም ብሎ ቃል ገብቷልና፡ በፍጹም አያደርገውም። እንደተናገረው... ቃል ገብቶ—በሌላ መለኩ እንደሚያደርገው ተሰፋ ሰጥቶ ሳለ? አላደርግም ብሎ ያለበት ምክንያት ይህ ነው።

እየተሰማኘ ነው። የሚሉትን አሳቦችን አታሰቡ። አያችሁ?

160 በዚህ መንገድ—አደርገዋለሁ ብሎ ተሰፋ ከሰጠ፡ ከዛ ውጪ በተቃራኒ ነገር ሁሉ አያደርግም። አያችሁ? በአሞጽ 3፡7 እንደተናገረው፡ በኦሪጂናል አሰራሩ ግን፡ በዚያ መንገድ ግን ይሰራዋል። ያም እውነት መሆኑን የተረጋገጠ እና የተመሰከረለት መሆን አለበት።

እንግዲህ፡ ዛሬም የሰጠን ተሰፋ ታውቃላችሁና፡ እንደተናገረውም ዛሬ እያደረገ ይገኛል። አደርጋለሁ ያለውም ያ ነው። ሰባት ማኅተሞች፡ እና ሌሎች የሚሰራቸውን ሁሉ ይከፍታል፡ ጥምቀትን እና ሌላውን ተበላሽቶ የነበረውን ሁሉ እያቃና፡ ሚስጢራትን ሁሉ ይገልጻል። አሁንም እነሆ፡ በገዛ መገኘቱ ነው። ሳይንሰም አረጋግጦታል። ሰማያት ሁሉ መሰክረውለታል። ሰዎች፡ ቆመው፡ እውን ሲሆን እያዩት ነው። እሱ ተናግሮ ያላደረገው አንዳች ነገር የለም። እናንተም ዛሬ ያለንበትን ማየት ትችሉ ዘንድ። ይኸው እዩት።

161 የእሱ መንፈስ በውስጡ ያለበት የትኛውም ሰው፡ በእርሱ ላይ የአምላክ መንፈስ ያለበት ሰው፡ ይህ ሁሉ እውነት እንደሆነ በትክክል ይረዳል፡ ምክንያቱ የጌታ መንፈስ ቃሉን የሚቃረን አይናገርም። በጭራሽ፡ አይናገርም። ከቃሉ ጋር አንድ ይሆናል እንጂ።

እናንተም፡ "እጮሃለሁ፡ በልሳን እናገራለሁ። በመንፈስ እዘላለሁና፡ መንፈስ ቅዱስ አለኝ" ትሉ ይሆናል። ይህ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ትርጉም የለውም። አያችሁ?

ዳዊትም፡ ያኔ በተግባር፡ እንዲሁ አድርጎ ነበርና። እሱ እና ከእርሱ ጋራ የነበሩት ሁሉ፡ በሙሉ ኃይላቸው ዘመሩ። እና በሙሉ ኃይላቸው ጮኹ፡ ሁሉም ግን ወደ ሞት እየወረዱ ነበር። እውነት ነው። ይህ ሁሉ ከዚህ ጋር በምንም አይገናኝም።

162 ዋናው ነገሩ ቃሉ ላይ ነው፡ የጌታ ቃል። "ጌታን የሚጠባበቁ ሁሉ።" አዎን፡ ወዳጄ። አያችሁ፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ሰዎች ሁሉ፡ የዘመኑን ተሰፋ ቃል ይጠባበቃሉ፡ እስኪያዩት ድረሰም ተግተው ይነቃሉ። በመጨረሻውም፡ እግዚአብሔር ይገልጥላቸዋል። "እርሱ ነው" ይላሉ።

163 እንደ ናትናኤል። ፊሊፖስ ወርዶ ናትናኤል አገኘው። ናትናኤልም "ቆይ እሰኪ፡ የተሰፋ ቃል እንዳለ አውቃለሁ፡ እስኪ እኔ ራሴ ልመልከተው፡" አለ። ካየው በኋላም፡ "እርሱ ነው፡" አለ።

ሴቲቱም አለች፡ "ብዙ አይነት፡ የሰነ መለኮት ምሁራን ሲናገሩ ሰምቻለሁ፡ አውቃቸዋለሁ፡ **ይሄን** እና ***ያንን*** አድርጌያለሁ። መጽሐፍ ቅዱሱን፡ በራሴ አንብቤአለሁ፡ የሚመጣ መሲሕ እንዳለ... አውቃለሁና፡ እነዚህ ነገሮችም ያደርጋልና፡ አንተም የእርሱ ነብይ ሳትሆን አይቀርም።"

እርሱም "እኔ እርሱ ነኝ፡" አላት።

164 እርሷም፡ “ይህ ሰው፡ ኑ እዩት፡ እርሱ ነው” አለች። መሲሑ በእግዚአብሔር ቃል ማየት እስክትችል ድረስ ጠበቀችው፡ ወድያው እንዲህ አለች፡ “ለአራት መቶ አመታት፡ ስንጠባበቀው የነበርነው ይህ ነው። ነቢይ ወይም ምንም ነገር ሳይኖረን ቆይተናል። እርሱ ነው፡ እራሱ ደግሞ እኔ ነኝ ብሏልና።” [በቴፑ ውስጥ ባዶ ቦታ—አርታዒ።] “... ያደረግኩትን ሁሉ የነገረኝ ሰው ኑና እዩት።”

ካህናቱ ግን እርሱን መግደል ፈለጉ፡ በመጨረሻም አደረጉት። አያችሁ?

ዛሬ ግን መንፈሱን መግደል አይችሉም። አዎ። አይ፡ መግደል አይችሉም። እኛን ወደ ውስጠኛው ለማስገባት እዚህ ነውና፡ እናመሰግነዋለን። አምላክ እንዴት ድንቅ እንደሆነ፡ ስራውም እዩት፡ እንዴት እንደማይወድቅ ተመልከቱት!

165 ስለዚህ፡ እግዚአብሔር ነገሮቹን የሚሰራበት የራሱ የመጀመርያ መንገድ አለው፡ ነገሮችን ለማድረግም በተቃራኒው ፈጽሞ አይሰራም።

166 በመጨረሻው ዘመን ይሄን አደርጋለሁ ብሎ ቃል ገብቷል። መልዕክቱም ላከ፡ ለእኛ ላከልን፡ መልዕክቱም ለኤልያስ እንደነበረው መለያ፡ አይነት መለያ አለው፡ ለኤልሳዕም የነበረው፡ መጥምቁ ዮሃንስም ጋር ነበረ። የህዝቡን ልብ፡ ወደ ሃይማኖት ተቋም አይመልስም፡ ነገር ግን ወደ መጀመሪያዎቹ፡ ወደ ሐዋርያት አባቶች፡ ወደ ቃሉ ይመልሳቸዋል። እነዚህ ነገሮች የተመሰከረባቸው ናቸው! ይህም በመጨረሻው መልአክ ድምጽ በሚሰማበት፡ ራእይ 10፡ “በሰባተኛው መልአክ ዘመን፡ ምስጢር ሆኖው የነበሩ ነገሮች ሁሉ... ”

“ሜቴዲስቶቹ **ይሄን** አደረጉትን፡ ባፕቲስቶቹስ፡ ቸርች ኦፍ ክራይስትስ፡ የጆሆቫ ምስክሮችስ፡ **ይሄን** ሁሉ አደረጉትን? ”

“ሚስጢራት ሁሉ በመጨረሻው ቀናት የሚገለጡ ናቸው፡ የሰባቱ መላእክት... የሰባተኛው መልአክ መልዕክት፡ እርሱ... ” ይህን ለመስራት መውጣት ሲጀምር ሳይሆን፡ “መልእክቱን ማሰማት ሲጀምር።” አያችሁ? እየተዘጋጁ ባሉ አመታት ሳይሆን፡ ነገር ግን፡ “የመልዕክቱ ድምጽ ሊያሰማ ባለው ጊዜ፡ ያኔ እነዚህ ምስጢራት ሁሉ ይፈጸማሉ።” እነዚህም እነሱ ናቸው፡ ሊያውቁት አልተቻላቸውም፡ እናንተ ግን የዚህ ነገር ምስክሮች ናችሁ።

167 በዚያ ታላቁ መቆጣጠሪ ጣብያ፡ የተከናወነ ነገር ምን እንደነበረ፡ ዓለም በታላቅ ግርምት ምን እንደተከናወነ ይገረማል። በቱሰን ባሉ፡ ታላላቅ መቆጣጠርያ ጣብያዎች ፎቶግራፉን አነሱትና፡ ምን እንደተፈጠረ ግን በጥያቄ ውስጥ ናቸው። “ምንድን ነው? ” እስከ አሁን ድረስ በጋዜጣ እስፍረዉታል፡ “ምን እንደተፈጠረ፡ እንዴት እንደሆነ የሚያውቅ ሰው አለ? ” በጠፈር ሰላሳ ማይልስ ከፍታ ላይ፡ ደመና በሌለበት፡ ንፋስ፡ እና እርጥበት በሌለበት ከፍታ ላይ። ኦህ፥ ማይ!

“በላይ በሰማይ ምልክት ይሆናልና። እነዚህ ነገሮች በሚከሰቱ ጊዜ፡ በብዙ ስፍራዎች የምድር መናወጥ፡ ያኔ የሰው ልጅ ምልክት፡ በሰማይ ላይ ይታያል።” በሉቃስ ላይ፡ “ያቺ ቀን፡” “የሰው ልጅ፡ ዳግም እራሱን ይገልጣል፡ እራሱን በሚገልጥበት ጊዜ።” ዓለም እንደ ሰዶም እና ጎሞራ ትመስላለች። ኦህ፡ ማይ!

ወንድሞች ሆይ፡ ስለ መንፈሳዊ ነገር የማታውቁ አትሁኑ፡ አያችሁ። “የዘለአለም፡ ዘለአለማዊ ህይወት በእነርሱ የምታገኙ ስለሚመስላችሁ፡ መጻሕፍትን ትመረምራላችሁ፡ እነርሱም ስለ ቃሉ ይመሰክራሉና።” ስለ

እውነትና፡ እግዚአብሔር አሁን ስለሚያደርጋቸው ነገሮች ሁሉ የሚመሰክሩ እነሱ ናቸውና።

168 አሁንስ ምንድን ነው? የአምላክ መንፈስ ያለቸው እነዚያ፡ ስለነዚህ ነገሮች ይጠባበቃሉ። እነዚያ ነግሮች ሲያዩአቸውም፡ ያምኑታል፡ ኢየሱስም፡ "አባቴ ካልሳበው በቀር አንድስ እንኳን ወደ እኔ መምጣት አይቻለውም። አባቴ የሰጠኝ ሁሉ ግን፡" "ወደ እኔ ይመጣሉ፡ ወደ እኔ ይመጣሉ።" እርሱም ቃል ነው።

169 ዛሬ ማለዳ ጠበቅ አድርጌዋለሁ፡ እያችሁ። ጌታን ይጠብቃሉ፡ ይጠባበቃሉ፡ ጠብቀውም፡ የዛሬውን ተስፋ ቃል ተፈጽሞ፡ እና ተረጋግጦ ሲያዩት፡ በቃሉ ውስጥ እምነታቸውን ያድሳሉ። ምክንያቱ፡ እንደሚያደርግ ቃል ገብቷል፡ ይሄውም እያደረገ ይገኛል። የሚያጠራጥር ነገርም የለም። እግዚአብሔር ይናገራል። መጀመርያ፡ ቃሉን፡ ይናገራል። በመቀጠል ቃሉ ይሆናል ብሎ ያመጣው ያ መንፈስ ራሱ እንደ ቃሉ ነገሮችን ያደርጋል።

አቤት፡ ብዙ አስመሳዮች አሉ። ገናም ብዙዎቹ ይመጣሉ፡ **እንዲህ** እና **እንዲያ** የሚያደርጉ ልበ ቅን ሰዎች ብዙ ይኖራሉ፡ ይሁን እንጂ ምን እንደሚሆን ተመልከቱ። ሰዎች እጆቻቸውን ያስገባሉ፡ ከዛዚያም——በኋላ ይሞታሉ። እያችሁ፡ አስተውሉት።

170 የትኛውም ሰው-ሰው ሰራሽ ተቋም ለራሳቸው በሰሩት የተቋም ታቦት፡ አባላትን ቢያበዙም በፍጹም አይሰራም። እግዚአብሔር የሃይማኖት ተቋም መቼም ኖሮት አያውቅም። ወደፊትም የሃይማኖት ተቋም አይኖረውም። ሰው-ሰራሽ ነገር ነውና።

171 ዛሬም ቢሆን፡ ከተቀዳንበት፡ ከታላላቅ ኮንፈረንሶቻችን እና ሪቫይቫል፡ በሜቴዲስት ታቦት፡ በባፕቲስት ታቦት፡ በፕሪስቢተርያን ታቦት ካልተሞላን ይደንቀኛል! የክርስቶስስ ታቦትስ፡ ቃሉስ?

ሙሽራይቱ ቃል ልትሆን ከተገባት፡ የሙሽራው ብልት ሆና፡ የክርስቶስ መሆን ይኖርባታል። ቃል ልትሆን ይገባታል፡ የሱ ዘመን ቃል ሳትሆን፡ በዚህ ዘምን እንዲገለጥ የመደበው፡ የዚህ ዘመን ቃል፡ ይህም ሙሽራውን ለመቅረጽ እና እሷን ለመሰራት የላከው ቃሉ ነው። እንዳየነው ተስፋ አደርጋለሁ! እንግዲህ የራሳችሁ፡ ወይም የሌላ ሰው አሳብ አትውሰዱ። የተረጋገጠውን፡ የመጽሐፍ ቅዱሱን ቃል ተቀበሉ። ይላልና።

እግዚአብሔር በዚህ በመጨረሻው ቀን ሙሽራውን እንዴት እንደሚመርጥ በቃሉ ቃል ገብቷል። ታውቃላችሁን? እንዴት እንደሚሰራ፡ ቃል ገብቷል፡ ክርስቶስን በሚመርጥበት፡ ዘመናት በሚመርጥበት፡ ወቅት በሚመርጥበት በኦርጂናል እቅዱ፡ እንደ እሱ… ሙሽራይቱ፡ የቃሉ አካል ስለሆነች፡ በፍጹም አይስታትም።

ክርስቶስን በሃይማኖት ተቋም ሳላልመረጠው፡ እሷን በሃይማኖት ተቋም አይመርጣትም። ክርስቶስ ወደ ሃይማኖት ተቋም መጣን? ወይስ ክርስቶስ በሃይማኖት ተቋም መጣን? የለም። እነርሱማ ተቃወሙት እንጂ። እንግዲህ፡ የሃይማኖት ተቋም የሚያደርገውም ድርጊት ይህ ነው። እንግዲያውስ ሙሽራይቱን ሲመርጥ፡ ከዚህ መንገድ ውጪ በሌላ ይመጣልን?

ክርስቶስን ወደዚህ እንዴት አመጣው? በነብያቱ ቃል። እውነት ነው? ሙሽራይቱንስ እንዴት ያመጣታል? በነብያት ቃል መሰረት።

በመጣስ ጊዜ መለያው እንዴት ይታወቃል? የኤልያስ መንፈስ በላዩ ላይ ሆኖ፡ ከምድረበዳ በሚወጣ ሰው። ሙሽራይቱስ መለያዋ ምንድን ነው? በሶዶም ጊዜ እንደነበረ፡ ምድርን ከማጥፋቱ በፊት፡ በሚልኪያስ ምዕራፍ 4 ላይ፡ ተሰፋ እንደሰጠው መልኩ።

172 ሶዶም እንደተቃጠለች አስታውሱ። አይደል? ይህች ዓለምም ደግሞ ትቃጠላለች። ኢየሱስም ተናግሯልና። በሉቃስ፡ ምዕራፍ 17፡ ከቁጥር 30 እንደተጻፈም ጊዜ ይሆናል፡ “የሰው ልጅ በሚገለጥበት ጊዜ፡ እንደ ሶዶም እና ጎሞራ ይሆናል።”

ከዛስ በኋላ ምን ይሆናል? በሚልኪያስ እንደተጻፈ፡ ምድርን ያቃጥላታል፡ ጻድቃንም ሁሉ (በሺው ዓመት) የክፉዎችን አመድ ላይ ይረግጣሉ። ትክክል ነው? አያችሁት?

ስለዚህ ያለነው በመጨረሻው ዘመን ነው። እሱ እንዲመጣ እየተጠባበቅን፡ በደጁ ላይ ቆመናል።

173 አስተውሉ፡ እግዚአብሔር ሙሽራውን... በመረጠው የመጀመሪያ መንገድ ሙሽሪትን እንደሚመርጣት በቃሉ ቃል ገብቷል። አስቀድሞ በነብያቱ አፍ ተናገረ፡ የተናገረውንም ለማሳየት እና ለማሳወቅ ነብይ ላከ።

ነብይውም፡ በዮርዳኖስ ዳርቻዎች ላይ ቆሞ “እነሆ፡” በማለት አውጇል!

እነርሱም “አንተ መሲሑ፡ አይደለህምን፡” አሉት?

እርሱም “እኔ መሲሑ አይደለሁም” አላቸው።

“አንተ’ማ መሲሑ ነህ።”

174 “እኔ እሱ አይደለሁም። እርሱ በመካከላችሁ አለ። እኔ ግን ጫማውን፡ ለመፍታት አልበቃም። ሲመጣ፡ ራሱን ያሳውቃል... ”

ዛሬም በመንፈስ ቅዱስ አምሳያ፡ ወደ ቤተክርስትያን በመምጣት፡ እራሱን አብዝቶ እየገለጠ እና እያስተዋወቀ በመካከላችን አለ፡ ወደ ቤተክርስቲያኑ እየመጣ፡ ራሱን እያሳወቀ፡ ምክንያቱም፡ እርሱ፡ እና ሙሽራና ሙሽራው አንድ ይሆናሉ፡ ራሱንም ያስታውቃል። አንድ ቀንም ያ በልባችሁ ውስጥ የተሞላችሁት ታዩታላችሁ፡ በፊታችሁ ደግሞ ስለሚቆም ምስሉንም ታውቃላችሁ፡ በእናንተ ፊት ይቆማል፡ እናንተ እና እሱ አንድ ናችሁ።

በቃሉ አንድ ሆናችኋል። ቃልም በመጀመርያ ስለ ነበረ፡ ወደ መጀመርያ፡ ወደ እግዚአብሔር፡ ይመለሳል። “በዛች ቀንም፡ እኔ በአባት እንዳለሁ አባትም በእኔ፡ እኔ በእናንተ፡ እናንተም በእኔ እንዳላችሁ ታውቃላችሁ።” ሃሌ ሉያ! እዚሁ አለን። ሃሌ ሉያ! በመካከላችን ሰብእናውን ሲገልጥ ማየቴ ደስተኛ ነኝ፡ ስለ ቃሉም የሰጠውን ተሰፋ ደግሞ እዩ፡ በአንዱ ስሜታዊነት፡ ዝማሬ፡ መዝለል፡ እና ማሽብሽብ ሳይሆን። ነገር ግን በገዛ ቃሉ፡ እራሱን ያስተዋውቃል፡ አሜን።

175 እዩ፡ መቅደስ ሰርተው፡ የቃልኪዳኑን ታቦት ወደሱ ባመጡ ጊዜ ግን፡ እግዚአብሔር በእሳት አምድ ወደ ውስጥ ገባ። አሜን። ያኔ ከአምላክ ፈቃድ ውጪ በነበሩ ጊዜ’ኮ፡ ዳዊት ነበር የሚዘለው እና የሚጮኸው፡ ዘማሪዎቹ እና

ክሃናቱ ነበር ነገሩን የሚያደርጉት። አሁን ግን እግዚአብሔር እራሱ የቃልኪዳኑን ታቦት አቅጣጫ እና ሰፍራ ሲያሰታውቅ ግን፡ ታቦቱን ወደዚያ ከማሰገባታቸው በፊት፡ መንገዱን የሚመራው የእሳት ዓምድ መጣ፡ የእሳቱ አምድ እራሱ በኪሩቤል ክንፎች ላይ፡ እና በማደርያው ላይ በቅድሰተ ቅዱሳን ጀርባ ሆኖ፡ መንገዱን መምራት ጀመረ፡ የእሳቱ አምድ! እንዴት ማገልገል እንደሚቻላቸው ማየት እሰኪሳናቸው ድረሰ-... የእግዚአብሔር ክብር፡ በሰፍራው ነበረ። አሜን።

ለሙሽራይቱ ሲመጣላት፡ የሰነ መለኮት ምሁራን አይን ሁሉ ይዘጋል። ለእነርሱ፡ እንደሆነባቸውም——በእኩለ ለሊት፡ ትወሰዳለች። ሰትሄድ በፍጹም አያዩዋትም። ኦህ፡ ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን!

176 አሰተውሉ፡ እግዚአብሔር ሙሽራይቱን እንደሚያሰወጣት፡ ምን እንደሚያደርግ ቃል ገብቷል። አንድ ዘር ይኖራል። ሲመሽ ብርሀን ይሆናልና፡ እነኚህ ነገሮች እንዴት ሊያደርጋቸው ነው፡ በትክክልም፡ በነገራችን ላይ ይህ ሁሉ የመጀመርያው ዕቅዱ በብሉይ እና በአዲሰ ኪዳን የነበረ ሐሳቡ ነው።

ሰለዚህ በኃይማኖት ተቋም አይደለም። ዛሬ እየሄድንበት ባለ ሰዋዊ ሰርዓት አይደለም። እኛማ ሞትን እያመጣን ነው። ሰዎች እጆቻቸው ሲከቱበት፡ በዛው ይሞታሉና። አያችሁ?

177 ቃሉ፡ የምሽቱ መልዕክት፡ የምሽት ውጤት ማፍራት አለበት። የምሽቱ መልዕክት፡ የማለዳ ዘር ሳይሆን የምሽት ዘር መዝራት አለበት። የምሽቱ ዘር! አይደል? የእኩለ ቀን እማ ሰራ፡ ዘሩም አልፎአልና፡ የተቋምም ነውና፡ ሞቷል፡ ጠፍቷል። የማምሻው-ጊዜ መልዕክት የማምሻው-ብርሃን ያሳያል፡ የማምሻ-ጊዜ ውጤት ያሳያል፡ የማምሻው-ጊዜ መልዕክት!

የኢየሱሰ ዘመን፡ የቀትር መልእክት፡ የቀትር ውጤቶችን አሳይቷል። የመጀመርያው መልእክት የመጀመርያ ውጤቶችን አሳይቷል፡ ፍጥረትን አደረገ። ልጁን በራሱ አምሳል ፈጠረ፡ በቀትር። በማምሻው ጊዜ ሙሽራይቱን አደረገላት። አያችሁ? በምን? በቃሉ።

ምድርን እንዴት ፈጠረ? ወደ መኖር እንዴት ተናገረ? በቃሉ!

ልጁ ማን ነበር? ቃሉ! "በመጀመሪያ ቃል ነበረ፡ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ። ቃልም ሥጋ ሆነ በመካከላቸውም አደረ።"

ሙሽራውን እንዴት ይወሰዳታል? በቃሉ፡ በአዲሰ ሰረገላ፡ ወይም በአንዳንድ ቲኦሎጂያን ሃሳብ አይወሰዳትም። ነገር ግን እንደ ቃሉ ይለያታል። አንዳች ነገር አትጨምሩ አንዳች ነገርም አትቀንሱ። እንዳለ ይሁን ተውት። አያችሁ?

178 ሲመሽ ጊዜ፡ እሱ እንደሚገለጥ ቃል ገብቷል፡ አብያተ ክርሰትያናቱ የሳቱት፡ የሰባቱ ማሕተሞች ጉዳይ በማምሻው እንደሚገልጸው ተሰፋ ቃል ገብቷልና። ራእይ 10፣ ሚልኪያሰ 4፣ ሉቃሰ 17፡30 ሁሉ፣ አደርጋለሁ ብሏል። እኛም አንቀላቅለው። ባለበት እንተወው።

179 እሰኪ ሰንጨርሰ... አሁን፡ እሩብ ጉዳይ ለአሰራ ሁለት እየሆን ነውና፡ እሰኪ፡ ይሄን በማለት፡ ልዝጋው።

ወዳጆች ሆይ፡ በጌታ በኢየሱሰ ሰም፡ አድምጡኝ! ይሄን ነገር አላምንም እንዳትሉ የተገለጠ እውነት ነው። አናይም እንዳትሉም በትክክል ግልጽ ነው።

በእውነት በትክክል ይታያቿል! ዓለምም ቢሆን በርግጥ የሚያየው ነገር ነው! የእናንተ ግን...

ዛሬ ዛሬ ባሉት እርባናቢስ ነገሮች አትወሰዱ፡ ምን ያህል መልካም፡ ምን ያህልም ቅኖች ሰዎች ቢሆኑ ግድ የለኝም። “እንደ ሕጉ እና እንደ ነብያቱ መሰረት ካልተናገሩ፡” መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው፡ “በእነርሱ ዘንድ ሕይወት የለም።” አያችሁ?

180 ዳዊት ቅን ነበረ። ትክክል ነኝ ብሎም አሰበ። ከሀናቱም ቅኖች ነበሩ። ትክክል ነን ብለውም አሰቡ። ይሁን እንጂ ጌታን ለማማከር አልቻሉም። ታድያ እንዴት ለማድረግ በቁ? ምናልባት፡ “ጸልየናል ብለው ይሆናል።” ይሁን እንጂ የጌታ አሰራር እንደዛም አይደለም። አስቀድሞ ለባሪያዎቹ ለነቢያት እስኪገልጥ ድረስ ምንም እንደማይሠራ ቃል ገብቷል። በመካከላቸው ደግሞ ናታን ቆሞ ነበር፡ ይሁን እንጂ በፍጹም አላማከሩትም።

181 ከዜና መዋእል ጥቂት ምዕራፎችን አንብቡና፡ ትረዱታላችሁ። ዳዊት በቤቱ ቆሞ፡ ናታንም አብሮት ቆሞ ሳለ፡ እንዲህ አለው፡ “ይህ ትክክል ነውን? ” “የጌታ ታቦት በድንኳን ላይ ሆኖ ሳለ፡ እኔ ከዝግባ—በተሰራ ቤት መኖሬ፡” ትክክል ነውን አለው? ናታንም፡ ማድረግ ያለበትን እንዲነግረው፡ ከጌታ ዘንድ ተቀበለ።

182 ጥፋትም ሰርቶ ስለነበረ፡ እግዚአብሔር እንዲህ በል አለው፦ “ባርያየ ዳዊትን እኔ ወደድኩት። በምድር እንዳሉ ታላላቅ ሰዎች ሰም አደረግኩለት፡ እንዲሰራልኝ ግን አልፈቅድለትም፡” እያህ፡ “አልታዘዘኝም፡” እየህ፡ “አልፈቅድለትም። ከልጆቹ መካከል ግን፡ ዘለአለማዊ የእግዚአብሔር ቤት የሚተክል ልጅ አስነሳለሁ።” በርግጥ፡ ያም ዳዊት ነበር። ሰለሞንም ጥላውን አደረገ፡ ይሁን እንጂ፡ እርሱም አልታዘዘም። ሁሉ መውደቅ ስላለበት። የሰው ዘር ሁሉ መውደቅ ስላለበት።

የማይወድቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው። አይወድቅም። እግዚአብሔር የማያደርጋት ብቸኛዋ ነገር፡ አለመውደቅ ናት። እግዚአብሔርም ቃል ነው። ቃሉም፡ በሌላ መንገድ የሚመጣ ምንም ቢመስልም፡ ቃሉ እንደሚናገረው አመጣጡም በዛው መልኩ ነው።

183 ወቅት እና ቀን፡ መከተል እንደሚገባችሁ፡ አስታውሱ። አያችሁ? ያንን እውነት መሆኑንም ለመረዳት፡ ምን አይነት ወቅት ነው፡ ምን አይነትስ ቀን ነው፡ ማረጋገጫውሰ።

184 አሁን ግዴታዎችን፡ ቃላቶቹን፡ ጥላዎቹን እና ነግሮቹን ሁሉ፡ አሰቧቸው፡ እናንተም ያላችሁበት ነገር መዝኑት። የምንኖርበትን ቀን አስቡት።

አሻግራችሁ ተመልከቱ፡ አንድ-አሰረኛው የምድር ክፍል ወደ ውስጥ ለመግባት ቀርቧል። ሳይንስ ይናገራል። ሰዓቱን እያዩ ነው። ከጥቂት ዓመታት በፊት፡ እንደተባለው፡ “ሦስት ደቂቃ ለእኩለ ለሊት ነው።” አሁን ምናልባት አንድ፡ ወይ ግማሽ ደቂቃ ይሆናል።

እነርሱ “በእኛ ትውልድ ላይ አይሆንም፡” ብሏል።

185 “በአምስት ደቂቃዎች ውሰጥ’ኮ ሊሆንም ይችላል።” ቀጥሎ የተናገርውም አስተውሉ፡ “አምስት አመት።” ይሄንን እኔ በፍጹም አላልኩም። እሱ እንጂ፡ ማለት ሳይንቲስቱ እንጂ። ልክ እንደ ዝንብ ከካሊፎርኒያ እየተመሙ

ናቸው። አያችሁ? እሺ፡ ሎጥ ከሰዶም የወጣ ለታ፡ በዛኑ ቀን እሳት ከሰማይ ወደ ምድር ዘነበ።

በነዚህ ቀናትም እግዚአብሔር መልዕክታችንን ይወስደዋል፡ እኛም ለቀን እንሄዳለን። በትክክል፡ አካሉ፡ ቤተክርሰትያኑ፡ ሙሽራይቱ፡ ከተወሰደች በኋላ፡ አንዳች ሊሆን ያለ ነገር አለ።

186 ቃል ላንብብላችሁ፡ እና እናንተም አብራችሁኝ እንድታነቡ እፈልጋለሁ። በመዝጊያችን ዘዳግም 4፡ እንድትከፍቱ እፈልጋለሁ። እንደሚመስለኝ እንድትረዱት የሚያስችላችሁ በቂ ነገር እንደተነገረ አሰባለሁ። ከዘዳግም 4። ሁለት ቦታዎች ላይ እነባለሁ።

ለእናንተም ለዚህ ቤተክርሰትያን፡ እንዲሁም ለቴፖቹ፡ በቴፕ ላላችሁ ሰዎች፡ እንዲሁም በመላ አገሪቱ በስልክ መስመር ለምትከታተሉ ሁላችሁ፡ እንዳያመልጣችሁ፡ በትክክል እንድትሰሙት እፈልጋቿለሁ። ይህ ነው እኔም...

በዘዳግም፡ 4ተኛ ምዕራፍ። 1ደኛው ቁጥር አነባለሁ። የመጀመርያው ቁጥር ላንብብ፡ እና ከ25ተኛ እስከ 26ተኛ ቁጥር ድረስ አነባለሁ። በቤታችሁ ሙሉውን ታነባላችሁ፡ አሁን ግን፡ ጊዜ ለመቆጠብ፡ ስለዚህ በጊዜ መውጣት እንድንችል፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ ዛሬ ማታ እንደገና መመለስ ስላለብኝ ነው። ይህ ነብዩ ምን እንደሚናገር ሰሙት። በእግዚአብሔር መገኘት ነበርና። የሚናገረው ሁሉ ያውቃልና። አድምጡት።

> **አሁንም እስራኤል ሆይ ሰማ፡ እንድታደርጉአቸው በሕይወትም** እንድትኖሩ፡ **የአባቶቻችሁም አምላክ እግዚአብሔር፡ ወደሚሰጣችሁ ምድር ገብታችሁ እንድትወርሱ፡ የማስተምራችሁን ሥርዓትና፡ ፍርድ ሰሙ። አሁንም ወጥታችሁ የአባቶቻችሁ አምላክ እግዚአብሔር የሚሰጣችሁን ምድር ውረሱ።** (የሺው አመት ጥላ ነው።)
>
> **እኔ ባዘዝኋችሁ ቃል** ላይ **አትጨምሩ፡ ከእርሱም** አንዳች **አታጎድሉበት፡** ("በእሱ ላይ አንዳች አትጨምሩ፡ እንዲሁም አንዳች አትቀንሱ። የሚናገረውን ብቻ፡ ትናገራላችሁ!") **እኔ ያዘዝኋችሁን የአምላካችሁን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ትጠብቁ ዘንድ።**
>
> **ጌታ** እግዚአብሔር... **በአል-ፌጎርን ያደረገውን ዓይኖችህ አይተዋል፡ በኣል-ፌጎርን የተከተሉትን ሰዎች ሁሉ አምላክህ እግዚአብሔር ከመካከልህ አጥፍቶአቸዋልና።** ("አሁንም እናንተ፡ ከሃይማኖት ተቋማት ሁሉ የተለየ ህዝብ ናችሁ።" አያችሁ? አያችሁ? )
>
> **እናንተ ግን ከአምላካችሁ ከእግዚአብሔር ጋር የተባበራችሁ፡** ዛሬ **ሁላችሁ ሕያዋን ናችሁ።** ("እናንተም አሁን ከሃይማኖት ተቋማችሁ አልሞታችሁም። በእግዚአብሔር ፊት፡ ህያዋን ናችሁ።")

ዝጉት፡ አትጥፉ። ቁጥር 25፡ አሁን፡ ወደ ምድሪቱ በወረዱ ጊዜ፡ የሆነውን ተመልከቱ።

> **ልጆችን የልጅ ልጆችን፡ በወለዳችሁ ጊዜ፡ በምድሪቱም...** ብዙ **ዘመን በተቀመጣችሁ ጊዜ በረከሳችሁም ጊዜ፡**

(የሆነውም ያ ነበርና)፡ **በማናቸውም ቅርጽ** (ሌላ ነገር)፡ **የተቀረጸ ምስል... ባደረጋችሁ ጊዜ፡ ታስቈጡትም ዘንድ በአምላካችሁ በእግዚአብሔር ፊት፡ ክፉ የሆነውን ነገር በሠራችሁ ጊዜ፡** (አዳምጡ!)

**እኔ ዛሬ** ሰማይንና **ምድርን በእናንተ ላይ አስመስክራለሁ፡** አያችሁ፡ **ትወርሱአት ዘንድ ዮርዳኖስን ተሻግራችሁ ከምትገቡበት ምድር፡** ወይም ከምድር ላይ፡ **ፈጽማችሁ ትጠፋላችሁ። ፈጽሞም ትጠፋላችሁ እንጂ፡ ረጅም ዘመን አትቀመጡባትም።**

187 ይህ ማለት፡ ሙሴ በእሳቱ አምድ፡ በአምላክ ከተመደበ በኋላ እና እነሱን መርቶ ለመውጣት የሚችል የአምላክ ባርያ መሆኑን፡ በእሳት አምድ ከተረጋገጠ በኋላ ሙሴ ለእስራኤል ህዝብ እየተናገራቸው ነው። ሙሴም፡ ወደ ምድሪቱ ከመሄዳቸው በፊት፡ ከመግባታቸው አስቀድሞ፡ "አሁን፡ በነገርሁህ ቃል፡ ሰማይንና ምድርን በአንተ ላይ ምስክር እጠራለሁ። ቅንጣት ያህል ብትቀንሱ፡ ወይም ብትጨምሩ፡ ጌታ እግዚአብሔር ለእናንተ በሰጣት ምድር አትቆዩም አላቸው።"

እኔም ደግሞ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ እንዲህ እላለሁ፡ በቴፑ ከተነገረው በቀር፡ አንዳች ነገር አትጨምሩ፡ አትቀንሱ የራሳችሁ ሀሳብ አትቀላቅሉ፡ ቴፕ ውስጥ የተቀዳውን ብቻ ተናገሩ፡ እንድታደርጓት ጌታ እግዚአብሔር ያዘዛችሁን ብቻ አድርጉ፡ አትጨማምሩ!

188 ሁሌም፡ ቃሉን ሙሉ ለሙሉ ጠብቆልናል። የገባልንን ቃል ሁሉ፡ ተብቋል። ይሆናል ብሎ የተናገረህ ነገር አለ፡ ሆኖአልን? እኔም ዛሬ፡ ሰማይን እና ምድርን ለሙግት በፊታችሁ እጠራለሁ፣ ጌታ አደርግላችኋለሁ ብሎ ያልፈጸመው ነገር አለን ያለውን በትክክል አላደረገልንምን? አደርገዋለሁ ባለው መንገድ አላደረገምን? ትክክል ነው። እንደዚሁም ይቀጥላል። አትጨምሩበት። አትቀንሱበት። በጌታ በአምላክህ ፊት በትህትና እየተጓዝክ እመን ብቻ፡ ወደ ምድሪቱ ለመግባት ተቃርበናልና።

ስለዚህ፡ መመለስ የለብህም፡ ወደ እንዲህ አይነት ህይወት መመለስ የለባችሁም። እንደማይሞት ፍጡር ትመለሳላችሁ እንጂ። ሰይጣን በሚታሰርበት ጊዜ፡ ኃጢአትም ባበቃለት ጊዜ፡ ያኔ ትመለሳላችሁ፡ አምላክህ እግዚአብሔር በሰጠህ ምድር ላይ አንድ ሺህ ዓመት ትኖራለህ። "ትሁታን ምድርን ይወርሳሉና።" "ከተማይቱ ውስጥ ለመግባት፡ ትእዛዛቱን የሚጠብቅ ሰው ብጹእ ነው።" "ጠንቋዮች፡ ኃሰተኞች፡ አምንዝራዎች፡ እና ውሾች አይገቡባትም። ሁሉም አይገቡም።" እነዚህ ለተዋጁት ብቻ፡ እና በትእዛዛቱ ለሚመላለሱ ናቸው።

189 እንግዳ ነገሮች አትቀበሉ። በየሰፍራው እየተባረሩ ናቸው፡ ገናም ደግሞ የሚመጡ ብዙ ናቸው። ይሁን እንጂ አዳዲስ ነገሮችን አትቀበል።

አምላክህ እግዚአብሔር እውነት የሆነውን ተናግሮሃል። አምላክህ እግዚአብሔር በቃሉና በመንፈሱ፡ እውነት የሆነውን አረጋግጧል። "በኃይል፡ እና በብርታት አይደለም፡ በመንፈሴ እንጂ።" መንፈሱም፡ "እግዚአብሔር፡ በመንፈስ እና በእውነት የሚያመልኩትን ይሻል።" "ቃልህ እውነት ነው።"

ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትም፡ ዛሬም፡ እስከ ለዘላለምም ያው መሆኑን አጥብቆ አረጋግጧል። የማምሻው ዘር ለእናንተ ገልጾታልና። በቃሉ፡ ለእናንተ ገልጾታል። በመንፈሱም ደግሞ፡ አረጋግጦላችኋል።

190 ተቋምን በፍጹም አትሞኩሩ አትጀምሩትም። በሌላ ለመስራት አትሞኩሩ።

በፋንታው ግን የተሰፋይቱ ምድር በሮች በቅርብ እንደሚከፈቱ ይመስላልና፡ በጌታ በአምላካችሁ ፊት ትሁታን ሁኑ። ከዛም በኋላ ሙሽራውና ሙሽራይቱ በዙፋኑ ላይ ስፍራቸውን ሲይዙ፡ በደስታ እና በእውነተኛ ዝማሬ እንግባ።

191 በትህትና ኑሩ። በፍቅር ኑሩ። እርስ በእርስ ተዋደዱ። በመኃላችሁ አንዳችህ ነገር አይግባ። ስለ አንድ ሰው አንዳችህ ነገር በልባችሁ መምጣጥ ሲጀምር ወድያው አሰወግዱት። አትፍቀዱለት...

ሰይጣንም ደግሞ በመካከላችሁ ለመግባት ይጥራልና። አያችሁ? አትድፍቀዱለት። ከስፍራችሁ እንዲነቅላችሁ ፈልጎ ምናልባት ጮሌ-አንደበት ያለው ወዳጅ ሊመጣባችሁ ይችላልና። ሙሴ ካየው እና ጸንቶ ቆሞበት ከነበረው ከአምላክ ህልውና፡ በንግግራቸው የሚያወጡት ይመስልሃልን? አይችሉም፡ ወዳጄ። አይችሉም። አንጨምር አንቀንሰም። ጌታ እንደተናገረው እንዲሁ እንጠብቀዋለን። ምንም አይነት የሃይማኖት ተቋም አንፈልግም። የትኛውም አይነት ድርጅት አንፈልግም። ምንም አይነት ምቀኛነት አንፈልግም። ምንም ሁከት አንፈልግም። የሚያስፈልገን እግዚአብሔር ነው፡ እርሱም ቃል ነው።

ራሶቻችን ዝቅ እናድርግ።

192 አምላክ ሆይ፡ ምን እየተካሄደ እንዳለ ለማየት፡ በመንፈሳዊ አይኖች ዙርያውን ለማየት ሞከርሁ። ከሰላሳ ሶስት አመታት በፊት ጀምሮ፡ እስከ ወንዙ ድረስ፡ የተናገርካቸው ሁሉ፡ ያልከውን አሁንም አስቀድሞ እንደተረጋገጠ፡ እና እንደ ጸና፡ እንደ-ቃልህ ሲሆን አየሁት። አሁንም ከሰላሳ-ሶስት አመታት በኋላ፡ አደርጋለሁ እንዳልከው ታደርጋለህ። እንዳልከውም እንዲሁ ታደጋለህ። ጌታ ሆይ፡ አንተን እየተከተልን በትህትና እንድንጓዝ እና አንተ ይሁን እንዳልከው፡ እንጠብቀው እንጂ፡ ለማሳነስ እና ለማተለቅ መሞከርስ ከእኛ የራቀ ይሁን።

193 ጌታ ሆይ፡ እነኚህ ሁሉ፡ ለዚህ አገልግሎት የሰጠሃቸው ናቸውና፡ ደግሞ በመላ አለምም፡ በአገሪቱም ጭምር ተኝተው ያሉ ሁሉ። እነዚህ መቃብሮችም፡ በመተባበቅ ያሉትን ከቅዱሳን ብዙዎችን ይዘዋል። ግን እንደተባለው ነው፡- “እኛ ህያዋን ሆነን ጌታ እስኪመጣ የምንቀር ያንቀላፉትን አንቀድምም። መለከቱ ሲሰማ፡ አስቀድመው ሙታን ይነሳሉ፡ አብረናቸውም እንነጠቃለን።” የእግዚአብሔር ክብር በምድር ላይ በሚሆንበት ጊዜ፡ ቤተክርስቲያንን ከአለም እንድትሰወር ያደርጋታል። ሰትወሰድም አያይዋትምና።

194 ጌታ አባት ሆይ፡ እነኚህ ሁሉ በመዳፍህ ውስጥ ሸሽጋቸው። የአንተ ናቸውና። አምላክ ሆይ፡ ዘወትር በፊትህ በትህትና እንድንጓዝ፡ እጸልያለሁ። ለምን ያህል ጊዜ እንደሆነ እናውቅም። ለምን ያህል እንደሆነም ማወቅ አንፈልግም፡ የኛ ጉዳይ አይደለም። ያ የአንተ ሰራ ነውና። መቼ እንደምትመጣ ለማወቅ የእኛ ፍላጎት አይደለም። ፍላጎታችን፡ ጌታ ሆይ፡ አንተ እስክትመጣ ድረስ፡ ትህትናን እንድንጠብቅ እና ከአንተ ጋር እንድንጓድ ነው። አባት ሆይ፡ ፍላጎታችን፡

በየጊዜው፡ አንተ በመካከላችን እራስህን ታስተዋውቅ ዘንድ፡ እኛም ከአንተ ጋር እንዳለን ማየት እንችል ዘንድ ነው።

195 ካለፈው ሐጢአቶቻችን ይቅር በለን። ወደፊትም፡ ከየትኛውም አይነት የዲያብሎስ ወጥመድ ጠብቀን እንዲሁም አቅናን። አቤቱ ምራን፡ አባታችን ሆይ ምራን። ኃጢአታችንን ይቅር በለን እና ልጆች እንድንሆን እርዳን። ምስኪን ህዝብ ነን። በዚህም አለም ማህበረሰብ፡ እና በአብያተ ክርስትያናት ተቋማት፡ የተጠላን ነንና።

መጨረሻውን እናያለን። የመጨረሻውን ጊዜ ለማየት፡ ወደ ቃልህ መንፈሳዊ እይታ ስላደረግክ እናመሰግንሃለን፡ እነኚህ ሁሉ ነገሮች ከሰማይ ወደሚሆን ወደ ታላቅ መደብደብ ይደርሳሉ። እርዳን፡ ጌታ ሆይ፡ በዚያች እለት፡ ወደ መገኛህ ወደ ጥልቅ እቅፍህ እንድንበር እንጂ፡ እዚህ እንዳንቀር እርዳን።

196 ጌታ ሆይ፡ የታመሙትን እና የተጠቁትን ፈውሳቸው። የማታውን ጉባኤ ድንቅ እንድታደርግልን እንጸልያለን፡ ጌታ ሆይ፡ ከአንተ መገኘት የተነሳም፡ በመሀላችን ደካማ ሰው አይኑር። ልባችን ሁል ጊዜ በአንተ የጸና ይሁን። ጌታ ሆይ፡ ገንዘብ፡ ንብረት፡ የአለም ነገሮች ሁሉ፡ ጊዜያዊና ትርጉም አልባ መሆናቸውን፡ እናውቃለን። ሁሉም ይጠፋሉ። ስራዎቻችን፡ ቤቶቻችን ሁሉ፡ ወዳጆቻችን፡ ሁሉ ጠፊ ናቸውና ይጠፋሉ። ምን ያህል ባለ ጸጋ፡ ድሃ፡ ታዋቂ፡ የማይታወቁ ብንሆንም የሁላችንም መሄድ የማይቀር ነው። እዚህ የመሆናችን ብቸኛ ቁምነገር አንድ ነው፡ እሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ስለዚህ፡ እግዚአብሔር ሆይ፡ ሁሉንም ነገር ወደ ጎን ትተን፡ እርሱን እንያዝ። እርሱም ቃል ነው። ባርከን፡ ጌታ ሆይ።

197 የተረጋገጠው እውነተኛ የዘመኑ ቃል! በሙሴ ዘመን የነበረ የተረጋገጠ የእውነት ቃል ኢየሱስ ነበረ። በኢሳያስ፡ ኤልያስ፡ ዮሀንስ፡ በሁሉንም ዘመን የነበረ የተረጋገጠ የዘመኑ ቃል፡ ኢየሱስ ነበረ። ዛሬም የተረጋገጠው ቃል ኢየሱስ ነው፡ ትላንትም፡ ዛሬም፡ ለዘላለምም ያው ነው። ጌታ ሆይ፡ ይህን እንድናይ፡ እንድናምነውም፡ በእርሱም እንድንሄድ፡ እርዳን። በኢየሱስ ስም—ጸለይን።

198 ራሶቻችን ዝቅ እንዳለ፡ ምናልባት ያንን እውነተኛ እና ታላቅ ውሳኔ አድርጎ የማያውቅ ሰው ካለ፡ ማወቅ እፈልጋሉ... እምነት ይኖራችኋል፡ ይሁን እንጂ ማመናችሁ በቂ አይደለም።

ሚስቴ'ኮ መልካም ሴት እንደነበረች አምናለሁ። እናት፡ አባትዋ አውቃቸዋለሁ። ለአመታት እና አመታት አውቃታለሁ። ንጹህ ህይወት የኖረች ሴት ናት። በጣም መልካም ሴት እንደነበረች ባውቃትም እንኳ፡ መልካምነትዋ ብቻ የእኔ እንድትሆን አያደርጋትም። እኔ እስክቀበላት፡ እሷም እኔን እስክትቀበለኝ ድረስ፡ በፍጹም የኔ አልነበረችም።

አሁንም ኢየሱስ ሊቀበላችሁ ይወዳል። እናንተስ ትቀበሉታላችሁን የቃሉስ አካል መሆን አትወዱምን? ራሳችሁ እና ልባችሁ ዝቅ እንዳለ፡ ይሄን ያልወሰናችሁ ከሆናችሁ፡ እንደ'ኔ...

199 ወደ መሰውያው ለመጥራት ስፍራ የለንም። ሲጀመርም፡ እኔ የምጠቅማቸው ነገር የለኝም። እግዚአብሔር ባላችሁበት እንደሚጎበኛችሁ አምናለሁ። እጃችሁን አንሥታችሁ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ በፀሎት አስበኝ። መቀበል እፈልጋለሁ፡” ትላላችሁን? ጌታ ይባርካችሁ። “እኔ... ” ጌታ ይባርካችሁ። አቤት፡ በየስፍራው እጆች ተነስቷል! “እንደዛ መሆን

እፈልጋለሁ።" ጌታ ይባርክህ፡ ወንድሜ። ተባረክ፡ ወንድሜ፡ ሁላችሁም፡ ተባረኩ። "መሆን እፈልጋለሁ።" ተባረኩ... "ተገንዝቤዋለሁ። እኔ—በእውነት እንደዛ መሆን እፈልጋለሁ።"

ወዳጄ ሆይ፡ ሰማኝ፡ ምናልባት፡ አሁን፡ ሌላ ነገር ይኖራል... እንደዛ ካልሆንክ፡ ከዛ ውጪ በዛ ዙርያ ቁምነገር ብለህ የያዝከው ሌላ ነገር አለ ማለት ነው። አሁን ግን በጣም ተጠግተኸዋል፡ እያየሀው ነው። አይተኸዋል። ለብዙ አመታት ከፍ ሲል፡ አይተኸዋል። አሁን አድጎ ታዩታላችሁ። ሁለመናችን ያ ከሆነ፡ ከዛ ውጪ ደግሞ ዘለአለማዊ ከሌለ፡ እንግዲያስ ታየው ከነበረ ነገር እራስህን መልሰህ ለምን ቁምነገርህ ሁሉ በእርሱ ዘንድ አታደርግም? የህይወት ሁሉ ቁምነገር፡ እርሱ ነው፡ የወደፊትም፡ እርሱ ነው። አብረን እየጸለይን፡ አትወስኑምን?

200 የተወደድክ ጌታ ሆይ፡ የወንዶች፡ እና የሴቶች የሰዎች፡ የእናቶች፡ እንዲሁም አገልጋዮች፡ እጆች ሁሉ፡ ወደ ላይ ተነሥቷልና። ህይወታቸው በጌታ በኢየሱስ ዙርያ ያተኮረ እንድትሆን—መናገር—ይፈልጋሉ፡ ይሁን እንጂ ያልቻሉ ይመስላሉ። ወደ **እዚህ፡** ወደ **እዚያ** አቅጣጫ የሚጎትታቸው ጎታች ነገር አለ። ምናልባት የሃይማኖት ትቋም፡ ወይም ሰው፡ ምናልባትም ኃጢአት፡ ምናልባት ደግሞ በልባቸው የደበቁት ነገር ይሆናልና። ጌታ ሆይ፡ እኔ አላውቅም። አንተ ግን ታውቃለህ። ምንም ቢሆንም፡ አሁን፡ ጌታ ሆይ፡ ሌሎች ሲጠሩህ... ጌታ ሆይ ጥራቸው። የአንተ ናቸውና።

አንተም ስትጠራቸው፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚል፡ ቶሎ ከሚከባቸው ሐጢያት፡ ይላቀቁ። "ቶሎ ከሚከበን ኃጢአት ርቀን፡ በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንድንሮጥ፡ ወደ ምን እያየን (ወደ ምን? ወደ ሥራችን? ወደ ኃይማኖት ተቋም? የተቆራኘናቸውን? ወደ ካውንስሎች?) እምነታችን በእርሱ ዘንድ ያለችውን ራስና ፈጻሚ ወደ ሆነው ወደ ክርስቶስ።" አባት ሆይ፡ ይህን ለእኛ አድርገው ዛሬ፡ ስለ ክብሩ ስለ ሰሙ፡ እንጸልያለን።

201 ጌታ ሆይ፡ አሁን የአንተ ናቸውና። መልካም ያልከውን አድርግባቸው። እኛም የአንተ ነንና። በጎ ነው ያልከውን አድርግብን። በኢየሱስ ሰም፡ አሜን።

እወደዋለሁ፡ እወደዋለሁ
ቀድሞ እርሱ ወዶኛልና
መዳኔንም ገዛሁ
በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

202 ስለ እራት ረሳችሁን? በመኪና ውስጥ ያሉ ልጆቻችሁ ደህና መሆናቸው፡ አለመሆናቸው፡ መጨነቅ ተዋችሁን? አሁን የሚሰማችሁ ምንነት እያስተዋላችሁ፡ ያለፈውን ነገር ሁሉ እየረሳችሁ ናችሁን? ቀን በቀን በአይኖቻችሁ ፊት፡ አካል ሲለብስ አይታችኋል፡ አያችሁ? ያ የሁሉ ነገራችሁ አንኳር ይሁን። ሌላው ነገር ሁሉ አርቁ፡ ሲጀመርም፡ ጠፊ ነውና።

ኦህ፡ ብቻ እርሱን ተከተሉት! አያችሁ? ኤልሳዕ ኤልያስን እንደተከተለ፡ እርሱን እንከተል። አንድ ቀን፡ በንጥቀት፡ እንወሰዳለንና። ከመቃብር ውስጥ ያነሱት የእሳት ሰረገሎችን ተመልክተናልና። አሁን በእኛ ዘንድ እንደሆነ ይሰማናልና። አንድ ቀን ግን ፈረሶቹን ከጫካው ይለቃቸዋል። ወደ ላይ እንሄዳለን። አትወዱትምን?

መዳኔንም ገዛሁ
በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

አቤት፡ ዝም ብላችሁ አይናችሁ እንደጨፈናችሁ ማዶ ላይ ተንጠንጥሎ አይታያችሁምን?

እወደዋለሁ፣ (ሌላ ማንን መውደድ እችላለሁ?) ወደዋለሁ
ቀድሞ እርሱ ወደኛልና
መዳኔንም ገዛሁ
በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

203 ሁሉ ጊዜ ወደ ቤት በተመለስኩ ቁጥር፡ አንድ ሰው አልፎ ይጠብቀኛል። ለጥቂት ወራት ወጥቼ፡ ስመለስ፡ አንድ ሰው ሂወቱ አልፎ ይጠብቀኛል። በመጣሁ ቁጥር አዝናለሁ።

በቀደም ለታ፡ አብሮኝ ትምህርት ቤት የተማርን ልጅ፡ በመንገዱ ላይ መጣና፡ "ሰላም፡ ቢሊ፡" አለኝ።

204 አየሁት እና፡ በጣም'ኮ ቆንጆ የነበረ ወዳጄ ነው፡ እውነተኛ የሆነ የሚያንጸባርቅ ወደ ኋላ የሚበጠር ጥቁር ጸጉር የነበረው፡ ሳየው ነጭ እንደበረደ ሆኗል። **እንዲህ** አይነት፡ ሸንቀጥ ያለ ሆድ ነበረው። አየሁት። "ሰላም፡ ጂም፡" አልኩት።

በልቤ፡ "ጌታ ሆይ፡ እኔ እና ያ ልጅ፡ እኔ እና ሰውዬው'ኮ፡ እኩያሞች ነን፡" ብየ አሰብኩ።

ያኔ፡ ቀኖቼ እንደተቆጠሩ አወቅሁ። ብዙ ሊሆኑ እንደማይችሉም ተረድቻለሁ። ዙርያየን ተመለከትኩና፡ አሰብኩ፡ "ጌታ ሆይ፡ ምን ማድረግ ይሻለኛል? አግዘኝ። አንተን ቀድሜ መጓዝ አልፈልግም። አንተ ምራኝ። አንተን—አንተን መከተል እሻለሁ።" ቆም አልኩና፡ አሰብኩት "ኃምሳ-ሰድስት አመቴ ነው፡ ኦህ፡ ማይ፡ ብዙ አልቆይም!"

205 ወደ ታች አየሁና፡ ውድ ወዳጄ ቢል ዳውች ቁጭ ብሎ አየሁት፡ ሰባ-ሁለት ወይም ሰባ-ሶስት አመቱ ነው። ዙርያየን ስቃኘው፡ እንዲህ የሚያስቡት፡ ህጻናት ይታዩኛል፡ "እስከ ወንድም ብራንሀም እድሜ ድረስ፡ እደርሳለን ብለው የሚያስቡትን፡ ብዬ ላስብ።" ውዴ፡ ምናልባት ላታዩት ትችላላችሁ። ማየታችሁን በጣም እጠራጠራለሁ። አያችሁ? ብቻ አስቡት፡ ወንድም ቢል ዳውች፡ እስከዚህ ቀን ድረስ ከኖረ፡ በየስአቱ እየረገፉ የሚገኙ። በመቶዎች-፡ የሚቆጠሩ፡ የአስራ-አምስት እና አስራ-ሰድስት አመት ታዳጊዎችን በልጦ ይኖራል።

ስለዚህ ዕድሜዎ ምንም ቢሆን ምን ልዩነት ይፈጥራል! ስለምትኖሩበት ዘመን ምን እየሰራችሁ ነው? በዚህ ጊዜ ለኢየሱስ ምን እያደረጋችሁ ነው? አያችሁ? አቤት፡ እሱን ማየት እፈልጋለሁ። የምመለከተውን ዘመን ማየት እና እነዚህ ሁሉ ያረጁ አካላት ሲለወጡ ማየት እፈልጋለሁ፡ "በቅጽበት አይን ሲለወጡ፡" ማየት እሻለሁ። ካልሆነ ግን፡ ከሁሉ በላይ ሞኝ ሰዎች ነን፡ በልተን፡ ጠጥተን፡ ተጋብተን፡ ነገ መሞት፡ መሞት፡ ከዛ በኋላ ወደ ቆሻሻ መጣል፡ እንዲህ ከሆነ እንስሳ ናችሁ። ነገር ግን ወንድሜ ሟች... ማለት የማይሞት ነፍስ፡ በውስጣቹ አለ። ከሰማያት ሰምተናል። ተረጋግጦም አይተናል። እርሱ በትእግስት የሚጠብቁትን፡ ዋጋ እንዲሰጥ አውቀነዋል።

የክርስቶስ አካል አባላት ሆይ፡ ደግመን፡ መዝሙር እየዘመርን ሳለ፡ በተቀመጣችሁበት ሆናችሁ እንደገና እየዘመርን በሰላምታ እጆቻችሁን እንድትጨባበጡ እፈልጋቿለሁ።

አይ...

ወንድም፡ እህታችሁን ሰላም በሉ።

እወደዋለሁ
ቀድሞ... (ሪቻርድ!)... ወደኛልና
መዳኔንም ገዛሁ
በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

206 ትወዱታላችሁን? “አሜን፡” እንበል። [ጉባኤው ሁሉ “አሜን፡” አለ።—አርታዒ።] ቃሉንስ ትወዱታላችሁን? “አሜን፡” እንበል። [“አሜን።”] ሐሳቡንስ ትወዱታላችሁ? “አሜን፡” እንበል። [“አሜን!”] አካሉንስ ትወዷታላችሁን? “አሜን፡” እንበል! [“አሜን።”] እንግዲያውስ፡ እርስ በእርስ ተዋደዱ። አሜን! በትክክል። “እርስ በርሳችሁ ፍቅር ሲኖራችሁ፡ ሰዎች ሁሉ የእኔ ደቀ መዛሙርት እንደሆናችሁ ያውቃሉ።”

እንግዲህ ከመምሸቱ በፊት ካገኛችኋቸው፡ እጆቼን በእነዚህ መኃረቦች እኑሬባቸዋለሁ።

207 ወንድም ሪቻርድ ብሌር እጋብዘዋለሁ... አምላክ እርሱ እና ያ ወንድሜ በቀደም እለት፡ ሲጸልዩ፡ እግዚአብሔር ጸሎታቸውን ሰምቷል፡ ይህም በእግዚአብሔር በማመናቸው፡ ይህን በመካከላችን ሕያው ሆኖ የተቀመጠ፡ ልጅ ዛሬ ይመልሱ ዘንድ ነበር። በጸሎት ቃል እንዲያሰናብተን እጋብዘዋለሁ፡ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ዛሬ ማታ መመለስ እንድንችል ነው።

ሰዓቱ፡ ልክ አስራ ሁለት ከአምስት ሲል። ዛሬ ማታ እዚህ ከሆናችሁ፡ እንድትመጡ፡ እጋብዛችኋለሁ። ወደ ቤት መሄድ ካለባችሁ፡ እግዚአብሄር መንገዳችሁን ያፍጥን፡ ይጠብቃችሁ፡ ይርዳችሁ። መቆየት ከፈለጋችሁ፡ መቆየት ከቻላችሁ፡ መቆየት ትችላላችሁ። ጌታ ከእናንተ ጋር ይሁን።

እስክንገናኝ! እስክንገናኝ!
ድረስ...

እጆቻችንን ወደ እርሱ እናንሳ።

... ኢየሱስ እግር አጠገብ፡
እስክንገናኝ! እስክንገናኝ!
እስክንገናኝ እግዚአብሔር ከናንተ ጋር ይሁን።

[ውንድም ብራንሀም **ጌታ ከእናንተ ጋር ይሁን** በውስጡ ዘመረ—አርታዒ።] ከእግዚአብሄር ቤት የምንሸኛኘው እንዲህ ነው፡ በጸሎት፡ በትህትና፡ ዛሬ ማታ እንደገና እንደምንገናኝ በማመን። ካልተገናኘንም፡ “እስክንገናኝ ድረስ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን!”

ራሳችንን ዝቅ እናድርግ። ወንድም ብሌር።

**ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ እግዚአብሔርን ለማገልገል መሞከር** AMH65-0718M

(Trying To Do God A Service Without Being The Will Of God)

ይህ መልዕክት በወንድም ዊልያም ማርዮን ብራንሃም በኢንግሊዘኛ የተላለፈ መልዕክት በ እሁድ ጠዋት፡ ሐምሌ 18፡ 1965፡ በዩ.ኤስ.ኤ.፡ ኢንዲያና፡ ጀፈርሰንቪል ከሚገኘው ከብራንህም ተበርናክል፡ ከማግኔቲክ ቴፕ ቅጂ ተወሰዶ ሳይሸራረፍ ወደ ኢንግሊዘኛ ተጽፏል። ይህ የአማርኛው እትም በቮይስ ኦቭ ጋድ ሪከርዲንግስ ተተርጉሞ ተሰራጭቷል።

AMHARIC

©2023 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS

P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.

www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ከፈለጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org